# የአገራችን የፖለቲካ ቀውስ መንስዔና መፍትሄ፣ በምክኒያታዊ አይን

## 1.መግቢያ

በአሁን ወቅት በአገራችን የተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ ለብዙዎች ድንገተኛና አስደንጋጭ ሆኗል፡፡ በእርግጥ ለአንዳንዶቻችን ክስተቱ አሳዛኝ ቢሆንም ድንገተኛና አስደንጋጭ ግን አልሆነም፡፡ እኔም ሆንኩ አባል የሆንኩበት ኢዴፓ በአንድ በኩል በተገቢው ወቅትና ሁኔታ እራሱን ማደስ ወይም መለወጥ የማይችል ማንኛውም መንግስት የመጨረሻ እጣ-ፋንታው በዚህ አይነት አስቀያሚ ሁኔታ ማለትም በአብዮትና በጠመንጃ ከስልጣን መውረድ መሆኑን ስለምንገነዘብ፤ በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነቱ አስቀያሚ የለውጥ ሂደት በአገራችን እንዳይከሰት በማሰብ የፅንፈኝነት ፖለቲካ ተወግዶ ምክንያታዊ የፖለቲካ ባህል በአገራችን እንዲፈጠር ለብዙ አመታት ያለ አድማጭ ስንጮህ ስለኖርን ለእኛ የወቅቱ ክስተት የሚጠበቅ አሳዛኝ ክስተት እንጂ ድንገተኛና አስደንጋጭ አልሆነም፡፡

የሆነ ሆኖ በአገራችን ለውጥ እንዲመጣ፣ የሚመጣው ለውጥ ግን የአገርን ህልውና ጥያቄ ውስጥ የማያስገባና እንዳለፉት የአገራችን የመንግስት ለውጦች አንድን ገዥ በሌላ ገዥ የሚተካ ሳይሆን እውነተኛ የስርዓትና የአስተሣሰብ ለውጥ እንዲሆን ለምንፈልግ ኃይሎች የወቅቱ ክስተት አስቸጋሪ አጣብቂኝ /dilemma/ ውስጥ የከተተን መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ አጣብቂኝ ውስጥ የገባነው ያለምክንያት ሳይሆን በአንድ በኩል በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት በእውነተኛ የህዝብ ምርጫ ስልጣኑን ለማጋራትም ሆነ ለመልቀቅ ፈቃደኛ የማይሆን አባገነናዊ መንግስት መሆኑን ከተግባራዊ ልምዳችን ጠንቅቀን ስለምናውቅ በሰላማዊ የህዝብ ትግል ተገዶ ለውጥን እንዲቀበል እንፈልጋለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በድርጅትና በመርህ ሳይሆን በስሜት፣ በምሬትና በጥላቻ እየተመራ ያለው ያልተቀናጀ የህዝብ ትግል መንግስትን ከስልጣን ከማውረድ አልፎ ጭራሹንም መንግስትና አገር አልባ ሊያደርገን ይችላል የሚል ከተጨባጭ ምክኒያት የመነጨ ስጋት ስላለን የወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ አስቸጋሪ አጣብቂኝ ውስጥ አስገብቶናል፡፡

መንግስት በአሁኑ ጊዜ በፖለቲካና በድርጅታው ጥንካሬ ረገድ ከመቼውም ጊዜ በላይ የተዳከመበት ወቅት ቢሆንም ከፀጥታ ኃይሉ አንፃር ግን ገና ያልተዳከመ ጉልበት ስላለው የወቅቱን ቀውስ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና በከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰትም ቢሆን ለጊዜው ሊቆጣጠረው ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ችግሩን ከምንጩ የሚያደርቅ አስተማማኝ መፍትሔ እስካልመጣ ድረስ ችግሩ ጊዜ እየጠበቀ በማመርቀዝ በአንድ ወቅት (ምንአልባት በጥቂት አመታት ውስጥ) ከቁጥጥር ውጭ መውጣቱ አይቀርም፡፡

በአሁኑ ወቅት መንግስት የተከሰተውን ቀውስ አስመልክቶ እያራመደው ያለውን አቋም በጥልቀት ካየነው የችግሩን መሰረታዊ ምንጭ በአግባቡ ሊረዳው አልቻለም፣ ወይም አልፈለገም፡፡ በዚህም ምክንያት ችግሩን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከምንጩ የሚያደርቅ የመፍትሄ አቅጣጫ መያዝ አልቻለም፡፡ በመንግስት በኩል የችግሩ መንስዔ ተደርጎ እየተወሰደ ያለው በዋናነት በመንግስት አመራር ዙሪያ የሚታይ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት፣ ከመልካም አስተዳደር ጋር የተያያዘ የአፈፃፀም ድክመትና የኢኮኖሚ ዕድገቱ የፈጠረው የህዝብ የበለጠ ተጠቃሚ የመሆን ፍላጎት ሲሆን፣ በመፍትሄነት የተቀመጠው አቅጣጫ ደግሞ (ገና በዝርዝር የቀረበ ባይሆንም) በጥቅሉ ሲታይ ጥልቅ ተሃድሶ በማካሄድ ኢህአዴግን እንደገና ጠንካራ ድርጅት ማድረግና የህዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚል ነው፡፡

ከዚህ የኢህአዴግ አመለካከት የሚመነጨውን ዝርዝር ጉዳይ ገና የምናየው ቢሆንም በችግሩ ምንነትም ሆነ መፍትሄነት ከተቀመጠው ከዚህ አጠቃላይ ሃሳብ መረዳት እንደምንችለው ግን ኢህአዴግ ያተኮረው ችግሩን ለጊዜው ማስታገስ በሚያስችሉ እና ጊዜ በሚገዙ መለስተኛ ጉዳዮች ላይ እንጂ ችግሩን በዘላቂነት ሊፈቱ በሚችሉ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ በችግሩ ምንጭነት በዋናነት የሚጠቅሰው ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ቢሆንም በእኔ አመለካከት ግን

መሰረታዊ የችግሩ ምንጭ ፖለቲካዊ ነው፡፡ ለወቅቱ የፖለቲካ ቀውስ ያበቁን ዋናዎቹ ምክንያቶች የፖሊሲ ስህተት፣ ከፍተኛ የመፈፀም ብቃት ማነስ፣ ስር የሰደደ ፀረ-ዲሞክራሲያዊነትና ትምክተኛነት ናቸው፡፡

ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ሊገኝ የሚችለውም ኢህአዴግ እንደሚለው ኢህአዴግን በጥልቀት በማደስ ብቻ ሳይሆን የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነውን ህዝብ እና የህዝቡን አስተሣሠብ በየደረጃው ሊወክሉ የሚችሉ ሲቪክ ማህበራትና የፖለቲካ ፓርቲዎችን የለውጥ ሂደቱ ሙሉ ተሳታፊና ባለቤት በማድረግ ጭምር ነው፡፡ የአገሪቱን ችግሮች መፍታት የሚቻለው በእኔና በእኔ አስተሣሠብ ብቻ ነው የሚለው የኢህአዴግ የትምክህት አመለካከት ጊዜው ያለፈበት ፀረ-ዲሞክራሲ አመለካከት መሆኑን የወቅቱ የህዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በግልፅ አሣይቷል፡፡ ኢህአዴግ እስካሁን በለመደው መንገድ ህዝብን እየገዛ ሊቀጥል እንደማይችል፣ ይህንን ተገንዝቦ ወደ እውነተኛ የለውጥ መንገድ በአስቸኳይ መግባት ካልቻለ እራሱንም ሆነ አገሪቱን ወደ ከፍተኛ አደጋ ይዞ በመግባት ያለፉትን ስርዓቶች ታሪክ ለመድገም እንደተዘጋጀ የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ቀውስ ግልፅ መልዕክት አስተላልፏል፡፡

ስለዚህ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ አገሪቱ ወደ እዚህ ዓይነት የተካረረ ቅራኔ ውስጥ የገባችበትን ምክንያት በዝርዝር ለማሳየትና በአሁኑ ወቅት ከፊታችን ከተጋረጠብን አደጋ አሻግሮ ወደ ዘላቂና አስተማማኝ የለውጥ ሂደት ውስጥ ሊያስገባን የሚችለው የመፍትሄ አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበት እንደ አንድ የፖለቲካ ተሣታፊ የሆነ ዜጋ በግሌ ያለኝን አመለካከት ለማጋራት ነው፡፡

## 2. የችግሩ መሰረታዊ ምንጭ ምንድን ነው? የመፍትሄ አቅጣጫውስ?

ለወቅቱ የፖለቲካ ቀውስ በዋናነት የዳረገን ከመንግስትና ከገዥው ፓርቲ የመነጨ ድክመት ቢሆንም መንግስትና ገዥው ፖርቲ ብቸኛ የችግሩ ምንጮች ናቸው ማለት ግን አይደለም፡፡ በእኔ አመለካከት መጠኑ ቢያንስም በተቃዋሚው የፖለቲካ ጎራና በህዝባችን ውስጥ ያሉ ከፖለቲካ ባህል ጋር የተያያዙ ድክመቶችም የችግሩ ምንጭ አካል ናቸው፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ በመንግስትና በገዥው ፓርቲ፣ ቀጥሎ በተቃዋሚው ጎራና በህዝባችን ዙሪያ የሚታዩትን ችግሮች ከነ የመፍትሄ አቅጣጫቸው በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር፡፡

## 2.1 የአሸናፊዎች ህገ-መንግስት

ከአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ጋር በተያያዘ ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን መሰረታዊ የአገራችን የፖለቲካ ቅራኔዎች ለመገንዘብ ከሞከርን መሰረታዊው ቅራኔ የአገሪቱን ማዕከላዊ የፖለቲካ ስልጣን በተቆጣጠረው ኃይል /center/ እና ከፖለቲካ ስልጣን ርቆ በሚገኘው ተቀናቃኝ ኃይል /perfery/ መካከል ያለ ቅራኔ ነው፡፡ ኢህአዴግና አጋሮቹ ለስልጣን የበቁበትን የ 1983 ዓ.ም ፖለቲካዊ ሁኔታም ካዬን ከአንድ መቶ አመት በላይ ከስልጣን ርቆ የፖለቲካ ተቀናቃኝ የነበረው የዳሩ ኃይል በማዕከላዊው የፖለቲካ ኃይል ላይ ያገኘው ድል ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ የሃይል ሚዛን ውስጥ የ 83 ዓ.ምህረቱን ለውጥ በዋናነት የመራው ህውሃት ከማዕከልና ከዳር /center-perfery/ የኃይል አሰላለፍ ረገድ ጣምራ ሚና ነበረው ማለት ይቻላል፡፡ ህውሃት የመነጨበት የትግራይ አካባቢ ላለፉት መቶ አመታት ከፖለቲካ ስልጣን ርቆ የዳር አገርነት የተቀናቃኝ ሚና የነበረው ቢሆንም በሌላ በኩል ግን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ከሌሎች የዳር አገር ተቀናቃኝ ኃይሎች በተሻለ የፖለቲካ ስልጣን ማዕከልነት ሚና የነበረው አካባቢ ስለሆነ በህገ-መንግስቱና በፌደራል አደረጃጀቱ አማካኝነት ኢትዮጵያዊነትን በራሱና በአጋሮቹ ምልከታ እንደገና ሊተረጉመውና ሊቀርፀው ቢሞክርም ሙሉ በሙሉ ሊያፈርሰው ግን አልፈለገም፡፡

ከ 83 ዓ.ም በኋላ ኢትዮጵያ ኤርትራንና የባህር በሯን ቀይ ባህርን ያጣች፣ ከአንድነት ይልቅ ለልዩነት የበለጠ ትኩረት የምትሰጥ ግዛትዋ ያነሳና ውስጣዊ አንድነቷ የላላ አገር ብትሆንም ቢያንስ ግን በአካባቢው የተሻለ ጠንካራ መንግስትና አንጻራዊ ሰላም ያላት አገር ሆና መቀጠል ችላለች፡፡ በ 83 ዓ.ምህረቱ ለውጥ የህውሃትን ሚና የያዙት ሌሎች የማዕከሉን ስልጣን ተጋሪ ሆነው የማያውቁ የዳር አገር ተቀናቃኞች ቢሆኑ ኖሮ ኢትዮጵያ የበለጠ ከመዳከም አልፋ አጠቃላይ ህልውናዋን ልታጣ የምትችልበት አደጋ ሊፈጠር ይችል ነበር፡፡

ነገር ግን ህውሃት ከመጀመሪያው ጀምሮ ኢትዮጵያን አንድ አድርጌ ለመግዛት እችላለሁ የሚል የተሟላ በራስ መተማመን ስላልነበረው በውስጡ የነበረውን ጥርጣሬና ስጋት የሚያንፀባርቁ ህግጋቶችና አሰራሮች በህገ-መንግስቱና በፌደራል አደረጃጀቱ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓል፡፡ አገሪቱን የዜጎች ሳይሆን የቡድኖች /ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች/ አገር ያደረገው ድንጋጌ፣ ቋንቋንና ብሄረሰብዓዊ ማንነትን መሰረት ያደረገው የፌደራል አደረጃጀትና ለእነዚህ የአገሪቱ ባለቤቶች እንዲሆኑ ለተደረጉ ቡድኖች የተሰጠው የመገንጠል መብት የህውሃትና አጋሮቹ ጥርጣሬና ስጋት መገለጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ኃይሎች ከእንግዲህ ያሸነፍነው ማዕከላዊ የፖለቲካ ኃይል ወደ ስልጣን ተመልሶ መምጣት የለበትም ብቻ ሳይሆን ተመልሶ መጥቶ ሊገዛን ከሞከረም የአገሪቱን ዕጣ-ፋንታ መፈረካከስ እናደርገዋለን በሚል የጠባብነት አመለካከት የአገሪቱን ህገ-መንግስት የአገራዊ መግባባት መገለጫ ሳይሆን የአሸናፊነት መገለጫ ሰነድ አድርገውታል፡፡ በዚህ ምክንያት በስልጣን ላይ የነበረው ማዕከላዊ የፖለቲካ ኃይል ብቻ ሳይሆን የዚህ ኃይል ማህበራዊ መሰረት የነበረው አካባቢ ህዝብ ከፍተኛ የተሸናፊነት ስሜት እንዲሰማውና ህገ-መንግስቱንና የፌደራል አደረጃጀቱን አገሪቱን የማዳከሚያና የማፍረሻ ስልት አድርጎ በጥርጣሬ የሚያይበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በተለይም የራሱን ማንነት ከኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር አንድና አንድ አድርጎ የማዬት ስነ-ልቦና ያለው የአማራው ህዝብና ከተለያዩ ብሄረሰቦች ተቀይጠው የተፈጠሩ የከተማ ነዋሪዎች ስርዓቱን ከመጀመሪያው በሙሉ ልባቸው የጋራችን ስርዓት ነው ብለው እንዳይቀበሉት አድርጓቸዋል፡፡ በእኔ እምነት ቀደም ሲል በአገሪቱ አንዳንድ ከተሞች፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በአማራው ክልል የተከሰተው የተቃውሞ እንቅስቃሴ በተለያዩ ወቅታዊና አካባቢያዊ ብሶቶች ሲቀባባ ቢታይም በዋናነት ስርዓቱን እንደ ስርዓት የእኔ ስርዓት ነው ብሎ ካለመቀበል የመነጨ ነው፡፡ የዚህ ህዝብ የተቃውሞ ስረ-መሰረት በዋናነት ከህገ-መንግስቱና ከፌደራል አደራጃጀቱ ጋር የተያያዘ ቢሆንም በሂደት የተከሰቱ የስርዓቱ ግፍና በደሎች አባብሰውት ዛሬ ላይ የደረሰበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል፡፡

ኢህአዴግ በህገ-መንግስቱና በፌደራል አደረጃጀቱ አማካኝነት የማንነት ጥያቄን መልሻለሁ ቢልም መመለስ የቻለው በራሱ መነፅር ብቻ ማዬት የቻለውን የራሱን የማንነት ጥያቄ ብቻ ነው እንጂ ማንነቱን ከኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር አንድና አንድ አድርጎ የሚያዬውን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠረውን ህዝብ ስሜትና ፍላጎት ግን በጥቅሉ በትምክህተኛነት አመለካከት በመፈረጅ ጨፍልቆት አልፏል፡፡ ለአለፉት 25 ዓመታት በአገሪቱ በብቸኝነት ሲራመድ የኖረው የስርዓቱ የፕሮፓጋንዳ ስልትም ለዚህ የኢትዮጵያዊ ማንነት ቦታ የነፈገም ብቻ ሳይሆን ማንነታቸውን ከኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር አያይዘው የሚያዩ ዜጎችን የሚያንቋሽሽና የሚያወግዝ ነበር፡፡

የማንነት ጥያቄን ከኢህአዴግ ቁንፅል ትንታኔ ወጣ ብለን ለማዬት ከሞከርን ግን ማንነት እንደዬ አንዳንዱ ብሄር ብሄረሰብ ብቻ ሳይሆን እንደዬ አንዳንዱ የአገር ዜጋ የግል ስሜትና ፍላጎት ሊተረጎም የሚችል ሰፊ ፅንሰ-ሃሳብ ነው፡፡ ነገር ግን ለአለፉት 40 ወይም 50 ዓመታት በአገራችን ከነበረው የፖለቲካ ውዝግብ /discourse/ አኳያ ማንነትን በሚመለከት ያሉት መገለጫዎች በዋናነት ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት መገለጫዎች ከፍ ሲል ልገልፀው ከሞከርኩት የማዕከልና የዳር /center-perfery/ የፖለቲካ ተቀናቃኝነት ጋር ተዛምደው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ላለፉት 100 ዓመታት ማዕከላዊውን የፖለቲካ ስልጣን ተቆጣጥሮ የኖረው የፖለቲካ ኃይልና በሱ የማንነት ትንታኔ ተቀርፆ ያደገው የህብረተሰብ ክፍል ኢትዮጵያዊ ማነነትን ከሁሉም

በላይ ገዥ አስተሳሰብ አድርጎ የሚያይና ከዚያ ውጭ ያሉ ከብሄረሰብ የማንነት ጥያቄ ጋር የተያያዙ የመብት ጥያቄዎችን ግን አሳንሶ ብቻ ሳይሆን የሌሉና የማይጠቅሙ አድርጎ የሚያይ ነው፡፡ ይህ ሃይል እስካሁን ድረስ ተገዶ ካልሆነ በስተቀር በመታወቂያ ካርዱ ላይ ብሄረሰብዓዊ ማንነቱ እንዲፃፉ ፍላጎት የሌለው መሆኑን እየገለፀ ያለ ነው፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ለአለፉት አንድ መቶ አመታት ከስልጣን ተገልሎ የኖረው የዳሩ ኃይል ከብሄር ወይም ከብሄረሰብ ጋር የተያያዙ የመብት ጥያቄዎችን ቀዳሚ የማንነት ጥያቄ በማድረግ ኢትዮጵያዊነትን ግን በሌሎች ተፅዕኖና ሚና የተሸከመው ዕዳ አድርጎ የሚያይ ነው፡፡ ይህ ኃይል ብሄረሰብዓዊ ማንነቱን ከኢትዮጵያዊነት አስቀድሞ ስለሚያይ ኢትዮጵያዊነትን በድርድር የሚያዝ አገራዊ ስያሜ እንጂ ከነጭራሹም ማንነት አድርጎ አያዩውም፡፡ በአጭሩ የማዕከሉ ኃይል የዳሩን ኃይል አስተሳሰብ "ጠባብነት" አድርጎ የሚፈርጀው ሲሆን የዳሩ ኃይል ደግሞ የማዕከሉን ኃይል አስተሳሰብ "ትምክህተኛነት" አድርጎ ይፈርጀዋል፡፡ ይህንን ዓይነት የማንነት ትንታኔ ተከትሎ የሚመጣ ፍረጃ ቢያንስ ለአለፉት 50 ዓመታት በአገራችን ዋና የፖለቲካ ቅራኔ መገለጫ ሆኖ ኖሯል፡፡

ጠባብነትና ትምክህተኛነት አሉታዊ ትርጓሜ ያላቸው የትችት መሰናዘሪያ ቃላቶች ሆነው ጥቅም ላይ ቢውሉም ዞሮ ዞሮ ከማንነነት ጥያቄ ጋር የተያያዘው የአገራችን የፖለቲካ ቅራኔ በሁለቱ ፅንፉ ውስጥ ያለ ነው፡፡ የሁላችንም አመለካከት በተወሰነ ደረጃ ሊከርና ሊላላ፣ ወይም ሊጠብና ሊሰፋ ቢችልም የማንነት ጥያቄን በተመለከተ ከእነዚህ ሁለት (የጠባብነትና የትምክህተኛነት) ፍረጃ ሊወጣ የሚችል አይደለም፡፡ እራሳችንን በዚህ መልክ አይተን ላናውቅ ብንችልም በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ አስተሳሰብ አሰላለፍ አንዳችን ለሌላችን "ጠባብ" ወይም "ትምክተኛ" ነን፡፡

አሉታዊ ትርጓሜውን ለጊዜው ወደ ጎን አድርገን ጠባብነትና ትምክህተኛነት በአገራችን ያለውን ከማንነት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ቅራኔ የሚያሳዩ መገለጫዎች አድርገን ብናያቸው የወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግስትና የፌደራል አደረጃጀት ጠባብነት በትምክተኛነት ላይ ድል ማግኘቱ የተረጋገጠበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ በመሆኑ በ 83 ዓ.ም የመጣው የስርዓት ለውጥ ቅራኔውን የአሸናፊነትንና የተሸናፊነትን ቦታ አቀያይሮ አስቀጠለው እንጂ ከቶውንም አላስቀረውም፡፡ ቅራኔው ሊታረቅ ይችል የነበረው ኢህአዴግ የማንነት ጥያቄን በተመለከተ የአንዱ ጎራ አስተሳሰብ ከሌላው ጎራ አስተሳሰብ ያነሰ ወይም የበለጠ፣ ትክክል ወይም ስህተት እንዳልሆነ ተገንዝቦ በአገሪቱ ህገ-መንግስትና የፌደራል አደረጃጀት የጠባብነትና የትምክህተኛነት አመለካከት ሚዛን በጠበቀ አግባብ ተቻችለው እንዲስተናገዱ ቢያደርግ ነበር፡፡

በኢህአዴግ ብቻም ሳይሆን በሁለቱም ጎራዎች ያለው መሰረታዊ ስህተት አንዱ የሌላውን የማንነት አመለካከት ስህተት አድርጎ በማዬት የራሱን አስተሳሰብ በሌላው ላይ ለመጫን መሞከሩ ነው፡፡ ነገር ግን ማንነታችንን የምንገልጽበት አመለካከት እንደዚሁ ስለፈለግነው በውሳኔ የያዝነው አመለካከት ሳይሆን ከቤተሰባችን፣ ከአካካቢያችን፣ በአጠቃላይም ከኖርንበት ማህበረሰብና ስርዓት ጋር በተያያዘ ተቀርፀን ካደግንበት እውነታ ጋር የተያያዘ ስለሆነ በማሸነፍና በመሸነፍ ወይም በማሳመንና በማመን ሊቀዬር የሚችል አይደለም፡፡ አንድ ወሊጋ ውስጥ ያደገ ኦሮሞ ከአንድ ጎንደር ውስጥ ካደገ አማራ፣ አንድ ሃመር ውስጥ ያደገ ዜጋ አንድ አዲስ አበባ ውስጥ ካደገ ዜጋ፣ አንድ ኡጋዴን ውስጥ ያደገ ሶማሌ ከአንድ አድዋ ውስጥ ካደገ ትግሬ ጋር የማንነት ጥያቄን በተመለከተ አንድ አይነት ወጥ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ማድረግ ፈፅሞ አይቻልም፡፡ መፍትሄው ይህንን ዕውነት ባለበት ተቀብለን በእኩልነትና በአንድነት አብሮ ሊያስኖረን የሚያስችል የጋር ቀመር /common ground/ መፈለግ ነው እንጂ በአሸናፊነትና በተሸናፊነት መንገድ ችግሩን ልንፈታው አንችልም፡፡

በህገ-መንግስቱና በፌደራል አደረጃጀታችን ውስጥ ያለውን ይህንን መሰረታዊ ጉድለት ሳንፈታ ህገ-መንግስቱን እንደ ምልኡ ሰነድ ወስደን ማባሪያ በሌለው የሰላምና የዲሞክራሲ ኮንፈረንስ፣ ወይም የሙህራን ትንታኔ የአንዳችንን ማንነት በሌላው ላይ ለማስረፅ መሞከር የሚያስገኘው ውጤት አይኖርም፡፡ ኢትዮጵያዊነቱን የማንነቱ ዋና መገለጫ አድርጎ የሚያዩውን ህዝብ ማሳመን የሚቻለው በህገ-መንግስቱና በፌደራል አደረጃጀታችን ውስጥ የብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር ጉዳይ ዋስትና

እንዳገኘው ሁሉ ለኢትዮጵያዊ ማንነትም አስተማማኝ ዋስትና በመስጠት ነው እንጂ በማስረፅ ዘመቻ አይደለም፡፡ ፌደራላዊ አደረጃጀት ለአገራችን አስፈላጊ መሆኑና የብሄር-ብሔረሰቦች መብት ሕገ-መንግስታዊ ዋስትና ማግኘቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ አገራዊ አድነት ቀጣይነትና ኢትዮጵያዊ ማንነትም በዚያው መጠን ሕገ-መንግስታዊ ዋስትና ማግኘት አለበት፡፡ ይህ መሰረታዊ የአገሪቱ ከፊል ህዝብ ጥያቄ ህገ-መንግስታዊ መልስ ሳያገኝ የአገራችን የፖለቲካ ችግር ዘላቂ መፍትሄ ያገኛል ብሎ ማሰብም ዘበት ነው፡፡

ስለዚህ ኢህአዴግ ህገ-መንግስቱ ያለበት ችግር የአፈፃፀም ችግር ነው ከሚለው ጠባብ የአስተሣሠብ ሳጥን ወጣ ብሎ የአገሪቱ ህገ-መንግስት ከወቅቱ የአገራችን ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም የማድረግ መፍትሄም ማሰብ አለበት፡፡

እዚህ ላይ አንድ መሰረታዊ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ኢህአዴግም ሆነ ተቃዋሚዎቹ በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ ህገ-መንግሰቱን እንዲያሻሽለው ለምን ይጠየቃል? ህገ-መንግስቱን የማሻሻል ጉዳይ ለምን ወደፊት በህዝብ ምርጫ ኢህአዴግን ለሚተካው መንግስት አይተውም የሚል ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ በአንድ በኩል ኢህአዴግ የማላምንበትን ህገ-መንግስት ለምን አሻሽለዋለሁ ብሎ ሊያስብ ስለሚችል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚው ጎራ ቀዳሚው ጥያቄ የኢህአዴግ ከስልጣን መውረድ እንጂ የህገ-መንግስቱ መሻሻል አይደለም ብሎ ከማሰቡ ሊነሳ ይችላል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች አግባብነት ያላቸው መስለው ቢታዩም ህገ-መንግስቱን የማሻሻል ጥያቄ መነሳትም ሆነ መልስ ማግኘት ያለበት በኢህአዴግ ዘመን እንዲሆን የሚመረጥበት አንድ እውነት መኖሩን ግን ማወቅ አለብን፡፡

የወቅቱ የአገራችን ህገ-መንግስት የተቀረፀው ኢህአዴግን በምርጫ የሚተካው መንግስት እንዳያሻሽለው ተደርጎ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱ ሊሻሻል የሚችለው በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የጋራ ይሁንታ ብቻ ስለሆነ ሁሉንም ክልሎች ከኢህአዴግና ከአጋር ድርጅቶቹ ቁጥጥር ውጭ የሚያደርግ የምርጫ ውጤት እስካልተገኘ ድረስ ህገ-መንግስቱ ሊሻሻል አይችልም፡፡ የሁሉንም ክልሎች ይሁንታ ሳያገኝ ለመንግስትነት የሚበቃ ፓርቲ ከህገ-መንግስታዊው አካሄድ ውጪ ሕገ-መንግስቱን በተፅእኖ ወይም በሃይል ለማሻሻል ከሞከረም ሊከተል የሚችለው ውጤት የአገር መፈራረስ ይሆናል፡፡ ይህንን እውነታ ግምት ውስጥ በማስገባት እራሱንና አጋር ድርጅቶቹን አሳምኖ ህገ-መንግስቱን የማሻሻል ታሪካዊ ኃላፊነት በኢህአዴግ ዕጅ ያለ ነው፡፡ ኢህአዴግ ሆን ብሎ እንዳይሻሻል አድርጎ የቀረፀውን ህገ-መንግስት እራሱ እንዲሻሻል የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢህአዴግ በአለፉት 25 ዓመታት የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታም ሆነ የኃይል አሰላለፍ በይዘትም ሆነ በቅርፅ እየተቀየረ መምጣቱን አውቆ የህገ-መንግስቱ አጠቃላይ ይዘት ከወቅታዊ ሁኔታዎቻችን ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እየተፈጠረ ያለው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ በግልፅ እየታዬ የመጣና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የዛሬ 25 ዓመት ከነበርንበት ሁኔታ በተለዬ ጠባብነትና ትምክህተኝነት ቦታ ተቀያይረዋል፡፡ የጠባብነት አጀንዳ ይዞ ለስልጣን የበቃው ኢህኢዴግ የዛሬ ቁንጮ ትምክህተኛ፤ በትምክህተኛነት አመለካካት ሲከሰስና ሲወገዝ የኖረው ተቃዋሚው ጎራ ደግሞ የጠባብነትን አጀንዳ የራሱ አድርጎ በመውረስ ስርዓቱን የማፈራረሻ መሳሪያ አድርጎ ሲጠቀምበት እያዬን ነው፡፡ የጠባብነትና የትምክህተኛነት አመለካከት ቦታ እየተቀያየሩና አሸናፊና ተሸናፊ እየሆኑ አገር የሚያፈራርሱበትን ሂደት የሚያስቆም የህገ-መንግስት ማሻሻያን አስፈላጊና ወቅታዊ የሚያደርገውም ይኸው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ነው፡፡

ሌላው ከህገ-መንግስቱ ጋር በተያያዘ የመወያያ ነጥብ መሆን ያለበት ጉዳይ የፓርቲዎች የብሄር አደረጃጀት ነው፡፡ ህገ-መንግስቱ የአገሩን ባለቤቶች ዜጎች ሳይሆኑ ብሄር-ብሄረሰቦች እንዲሆኑና የአገሪቱ ፌደራላዊ አደረጃጀት መስፈርት በዋናነት ቋንቋ እንዲሆን ያስገደደው የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የተደራጁት አገራዊ አስተሳሰብን መሰረት አድርገው ሳይሆን ብሄረሰባዊ ማንነትን መሰረት አድርገው በመሆኑ ነው፡፡ የህገ-መንግስቱ ይዘትም ሆነ የፌደራል አደረጃጀቱ መስፈርት በዋናነት እንዲጣጣም ተደርጎ የተቀረጸው ከአገሪቱ መሰረታዊ ችግሮች ጋር ሳይሆን ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ብሄረሰባዊ አደረጃጀት ጋር ነው፡፡ ይህ በአሸናፊው ሃይል የተመረጠ አደረጃጀት አገራዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ከስርዓቱ ልዩ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን፣ ከዚህ በተጻራሪ

የመሃል አገሩ ህዝብ ምርጫ የሆነው ህብረ-ብሄራዊ የፓርቲ አደረጃጀት ግን እንደ ትምክህተኛነት መገለጫ ተቆጥሮ የትችትና የጥቃት ኢላማ ሆኖ ኖሯል፡፡ ኢህዴንም ከኢትዮጵያዊ ድርጅትነት ወደ አንድ ብሄር ድርጅትነት ተቀይሮ የአማራ ህዝብ ወኪል እንዲሆን የተደረገው የአማራው ህዝብ የብሄር አደረጃጀትን ስለመረጠ ሳይሆን ወደደም ጠላም የግድ ከህገ-መንግስቱና ከፌደራል አደረጃጀቱ ጋር ተጣጥሞ እንዲደራጅ ስለተፈለገ ነው፡፡

በእኔ አመለካከት ህዝቡ ከአካባቢያዊ ጉዳዮች ባለፈ በወደፊት የጋራ ዕጣ-ፈንታው ላይ እንዳያተኩርና አገሪቱም ወደ አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ እንዳትሸጋገር ያደረጋት ብሄረሰባዊ አደረጃጀት የስርዓቱ ተመራጭ አስተሳሰብ መሆኑ ነው፡፡ በብሄር ወይም በብሄረሰብ ማንነት መደራጀት አንዳንድ አገሮች እንደሚያደርጉት ህጋዊ እገዳ ሊጣልበት ይገባል ብዬ ባላምንም ከብሄር አደረጃጀት ይልቅ አገራዊ አጀንዳን መሰረት ያደረገ ህብረ-ብሄራዊ አደረጃጀት በአገራችን የበለጠ ትኩረትና ቦታ ቢያገኝ አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ የመፍጠር ፍላጎታችንን በተሻለ ፍጥነትና ሁኔታ ሊያሳካው ይችላል፡፡

አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ በመፍጠር የኢትዮጵያን ህዳሴ አሳካለሁ የሚለን ኢህአዴግ በቅድሚያ ራሱን ወደ አንድ ውህድ የአስተሳሰብ ፓርቲ ሳይቀይር ኢትዮጵያን ወደዚያ የላቀ ደረጃ ሊወስዳት የሚችልበት ዕድል የለውም፡፡ የብሄር አደረጃጀት ገዢ አስተሳሰብ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ የበለጠ ልዩነታችን እየሰፋ እንጂ አንድነታችን እየጠነከረ ሊመጣ አይችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን እንደሚታየው መቼም ቢሆን ይቆማል ተብሎ በማይታሰብ ሁኔታ ቀበሌዎች ወረዳ፣ ወረዳዎች ዞን፣ ዞኖች ክልል፣ አንዳንድ ክልሎችም አገር ለመሆን እያቀረቡት የሚገኘው አታካች ጥያቄ እያሳየን ያለው በአገራችን የህዝቦች አንድነት ሳይሆን ልዩነት የበለጠ እየተጠናከረ መምጣቱን ነው፡፡

## 2.2. ህገ-መንግስት እንጂ ህገ-መንግስታዊነት የሌለው ስርዓት

ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት ማዕከላዊው ኃይል ህገ-መንግስቱን ከጅምሩ የኔ ነው ብሎ ያልተቀበለው ቢሆንም አሸናፊው የዳር አገሩ ኃይል ግን ህገ-መንግስቱን ከጅምሩ የራሱ አድርጎ ተቀብሎት ነበር፡፡ ይህ ኃይል ከእንግዲህ በኋላ የመብት ጥያቄዬ በሌሎች ኃይሎች እንዳይሸራረፍና እንዳይታፈን ህገ-መንግስቱ ዋስትና ሰጥቶኛል ብሎ በማመን ራሱን የህገ-መንግስቱ ጠባቂና ባለቤት አድርጎ ማዬት ጀምሮ ነበር፡፡ የዳር አገሩ ኃይል ብቻ ሳይሆን ማዕከላዊው ኃይልም በህገ-መንግስቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ አንቀፆችን አምርሮ ቢጠላም በህገ-መንግስቱ ውስጥ ያሉ ከዲሞክራሲና ከሰብዓዊ መብት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎች በአግባቡ ከተከበሩ መብቴን ለማስከበር ብቻ ሳይሆን ስርዓቱንም በሰላማዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ ታግዬ ለመቀዬር መሳሪያ ሆነው ሊያገለግሉኝ ይችላሉ የሚል ተስፋ ነበረው፡፡

ነገር ግን በሂደት እንደታዬው ስርዓቱ ህገ-መንግስት ከማውጣት ባለፈ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት መሆን ስለተሳነው የማዕከሉንም ሆነ የዳር አገሩን ኃይል፣ ማለትም የአሸናፊውንም ሆነ የተሸናፊውን ፍላጎት ማሟላት አልቻለም፡፡ ኢህአዴግ ህገ-መንግስቱንም ሆነ የፌደራል አደረጃጀቱን እንደራሳቸው አጀንዳ የተቀበሉትን ኃይሎች መብት በፓርቲ ማዕከላዊነትና በሞግዚት አስተዳደር ጠልፎ በመውሰድ ህገ-መንግስታዊ መብታቸው ትርጉም አልባ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ህገ-መንግስቱ መሰረታዊ የሰው ልጅ መብቶች እውቅና እንዲያገኙ ከማድረግም አልፎ ለብሄር-ብሄረሰቦች ከአገር እስከመገንጠል የሚደርስ መብት በመስጠት በአለም ለጋሱ ህገ-መንግስት ተብሎ የተሞካሸ ቢሆንም በተግባር መሬት ላይ ያለው እውነት ሲታይ ግን ስርዓቱ ከንጉሱና ከደርግ ስርዓትም በባሰ ስልጣን በአንድ ፓርቲ፣ ከዚያም አልፎ በአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ስር የወደቀበት የተማከለ ስርዓት ሆነ፡፡ በህገ-መንግስቱ ውስጥ ደምቆ የተፃፈው የህዝብ የስልጣን ባለቤትነት እንኳንስ በወጉ ሊከበርና የፖለቲካ ድርጅቶች እየፈጠረ ለህዝብ የሚያድለው፣ ማናቸውንም ዓይነት የፖሊሲ ውሳኔዎች እየደነገገ በካድሬዎቹ አማካኝነት ቁልቁል ወደ ህዝቡ የማስረፅ ስራ የሚሰራው አራት ኪሎ የሚገኘው የኢህአዴግ ጽህፈት ቤትና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ሆነ፡፡ እንኳንስ ራስን በራስ

የማስተዳደርና የመገንጠል መብት መሰረታዊ የሚባሉት የመደራጀትና ኃሳብን የመግለፅ መብቶችም ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉት የገዥውን ፓርቲ ፍላጎትና ጥቅም እስከ ደገፉ ድረስ ብቻ እንደሆነ በገሃድ ታዪ፡፡

አስራ ሰባት አመት በተካሄደ መራራ ጦርነት ለብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ታግያለው የሚለው ኢህአዴግ ራሱን በመንግስት ስልጣን ላይ ካቆናጠጠ በኋላ ግን አኒማል-ፋርም /Animal-farm/ በተሰኘው የጆርጅ ኦርዌል መፅሃፍ ላይ በመሪ ተዋናይነት የሚተውነውን ዓሳማ ዓይነት ሚና መጫዎት ጀመረ፡፡ እንኳንስ ህገ-መንግስቱን ከጅምሩ ያልተቀበሉትን ኃይሎች የህገ-መንግስቱ ዋና ባለቤትና ተጠቃሚ ናቸው የተባሉትን ኃይሎችም መብት ሳያከብር ቀረ፡፡ በተለያዩ ወቅታዊና አካባቢያዊ ጉዳዮች እየተቀባባ የሚቀርብ ቢሆንም ለአለፉት ዓመታት በዋናነት በኦሮሚያ ክልልና በተለያዩ የአገራችን የዳር አገር አካባቢዎች በመንግስት ላይ እየቀረበ ያለው የተቃውሞ እንቅስቃሴ በዋናነት የሚመነጨው ህገ-መንግስቱን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ የሚችል ህገ-መንግስታዊ ስርዓት መኖር ካለመቻሉ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱ መንግስትን ከሌሎች ጥቃት ለመከላከልና ሌሎችን ለማጥቃት በመሳሪያነት ጥቅም ላይ የዋለ የፖለቲካ መሳሪያ ከመሆን አልፎ ለህዝቡ ጥቅምና መብት መከበር ዋስትና ሊሆን አልቻለም፡፡

ህገ-መንግስቱ የአገርንና የህዝብን ዘለቄታዊ አንድነት በማስከበር ረገድ መሰረታዊ ጉድለቶች ያሉበት ሰነድ ቢሆንም አብዛኛው የህገ-መንግስቱ ክፍል ግን ለህዝቡ ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች መከበር ተገቢውን ዕውቅና የሰጠ ሰነድ በመሆኑ ቢያንስ ከነጉድለቶቹም በአግባቡ በተግባር የሚውልበት ሁኔታ ተፈጥሮ ቢሆን ኖሮ አገሪቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል በጎ ሚና በኖረው ነበር፡፡ ነገር ግን በወረቀት ላይ አምሮና ደምቆ ከመታዬት አልፎ ትርጉም ባለው ሁኔታ በተግባር ላይ ሊውል ባለመቻሉ የቡድኖችንም ሆነ የዜጎችን ፍላጎት ማርካት አልቻለም፡፡

በዚህም ምክኒያት በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ለሚታዬው ብጥብጥና የሰላም ዕጦት ዓይነተኛ መነሻ ምክኒያት ሆኗል፡፡ መንግስት በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ለገጠማት የፖለቲካ ቀውስ በምክኒያትነት የሚጠቅሳቸው የተለያዩ ጉዳዮች ቢኖሩም ህገ-መንግስቱ በይዘት ደረጃ ያለበትን ጉድለትም ሆነ የህገ-መንግስቱን በአግባቡ ተግባር ላይ አለመዋል በዋና ምክንያትነት ሊቀበለው አይፈልግም፡፡ በእኔ አመለካከት ግን በህገ-መንግስቱ ይዘታና ትግበራ ዙሪያ የሚታዩት ችግሮች እራሱ ህገ-መንግስቱ በሚፈቅደው አግባብ በሂደት ሊሻሻሉ የማይችሉ ከሆነ ከማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የሚታዩ የማዕከሉና የዳሩ የፓለቲካ ኃይሎች ቅራኔዎችም ሆኑ በመንግስትና በዜጎች መካከል የሚታዬው ቅራኔ በዘላቂነት መፍትሔ ሊያገኝ አይችልም፡፡

## 2.3. የመልካም አስተዳደር ዕጦት

ገዥው ፓርቲ መልካም አስተዳደርን የሚተረጉመው በራሱ መንገድ በቁንፅል ቢሆንም ለወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ችግር ዋናው ምክንያት እንደሆነ አምኖ ይቀበላል፡፡ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለመከበር ጉዳይ በአገራችን ዋናውና መሰረታዊው የመልካም አስተዳደር ችግር ቢሆንም ገዥው ፓርቲ በአገራችን የሚታዬውን የመልካም አስተዳደር ችግር የሚተረጉመው በዋናነት ከመንግስት መስሪያ ቤቶች የአገልግሎት አሰጣጥ ድክመትና ከሙስና ጋር አያይዞ ነው፡፡ ስለሙስናም ሲያወራ ስለኢኮኖሚያዊ ሙስና እንጂ ለኢኮኖሚያዊ ሙስና መስፋፋት መሰረቱ የፖለቲካ ሙስና መኖር መሆኑን አምኖ መቀበል አይፈልግም፡፡ ገዥው ፓርቲ በአገሪቱ የተከሰተውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት የሚሞክረውና የሚፈልገው መሰረታዊ ምንጬን ማለትም የፖለቲካ ሙስናን እንደ ዋና ምክንያት ሳይቀበልና ቅንጭብጫቢ አስተዳዳራዊ ችግሮችን በመፍታት ስለሆነ ችግሩን እስካሁን ሊፈታው ይቅርና ሊያቃልለውም አልቻለም፡፡ ገዥው ፓርቲ ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነገር እያሰበና እየሰራ የተለዬ ውጤት ላይ መድረስ የሚፈልግ ግብዝ ኃይል ስለሆነ ከፍተኛ የአገር ገንዘብ በማፍሰስ ለብዙ ዓመታት ያካሄዳቸው ተከታታይ የመዋቅር ማሻሻያዎች በሙሉ ትርጉም ያለው ለውጥ ሳያመጡ ከሽፈዋል፡፡

በአገራችን ያለው የፖለቲካ ሙስና ብዙ መገለጫዎች ያሉት ነው፡፡ ምርጫን ማጭበርበር፣ ሕዝብ ያላመነበትንና ያልመከረበትን ሕግና ፖሊሲ በላዩ ላይ መጫን፣ የተቃውሞ አስተሳሰብ ባላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ላይ የአፈና ድርጊት መፈጸም፣ ነጻና ገለልተኛ የሕዝብ ተቋማትን እያፈረሱ በጥገኛና አድሏዊ ተቋማት መተካት፣ የመንግስትን ተቋማትና ሃብት ለፓርቲ ጥቅም ማዋል፤ ዜጎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከመንግስት የሚገኝን ስራና ጥቅም ለማግኘት ሲሉ የፓርቲ አባልና ደጋፊ እንዲሆኑ ማስገደድ፣ የመንግስት መገናኛ ብዙሃንን እራስን ለማወደስና ሌሎችን ያለ አግባብ ለማጥላላት መጠቀም፣ ከህግ ውጭ የፓርቲ የንግድ ድርጅቶን እያቋቋሙ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ማዳከም፣ የገዥውን ፓርቲ ህልውና እስካልተቀናቀኑ ድረስ የመንግስት ሹማምንት በህዝብ ላይ የሚፈጽሙትን በደል በዝምታ ማለፍ  ወዘተ .... እነዚህ ሁሉ ለአለፉት 25 ዓመታት በዚህ አገር በጠራራ ፀሐይ ሲፈፀሙ የኖሩ የፖለቲካ ሙስናዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ፈርጀ ብዙ የፖለቲካ ሙስናዎች ሲፈፀሙ ዝም ብሎ ማየት ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካ ስልጣን የበላይነቱ ሲል በካድሬዎቹ አማካኝነት እንዲፈፀሙ ሲፈቅድና ሲያዝ የኖረ መንግስት፣ ዛሬ ካድሬዎቹ ከሱ የፖለቲካ ሙስና ተምረው የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን የኑሮ ህልውና ለማስጠበቅ ሲሉ የኢኮኖሚ ሙስና ቢፈፅሙ ሊያስገርም አይችልም፡፡ እንደዚህ በፖለቲካ ሙስና የተዘፈቀ መንግስትም የኢኮኖሚ ሙስናን ተዋግቶ ለማሸነፍ የሚያስችል ሃቀኛ ፍላጎት፣ አቅምና የሞራል ብቃት ሊኖረው አይችልም፡፡

በዚህም ምክንያት የመልካም አስተዳደር እጦት ለሕዝቡ ብሶትና ምሬት መባባስ አንዱ አንገብጋቢ ምክንያት ሆኗል፡፡ ህዝቡ መንግስት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች አድማጭና ፈጻሚ የመሆን እንጂ ትርጉም ያለው የተሳትፎ መብት የለውም፤ ዲሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ የመንግስት ሹማምንትን የመምረጥና ሰብአዊ መብቱን ከጥቃትና ከአፈና የመከላከል መብቱን በካድሬዎች ተነጥቋል፤ ለአመታት ደጅ ሳይጠና ወይም ጉቦ ሳይሰጥ ጉዳይ ማስፈጸምም ሆነ ፍትህ ማግኘት ተስኖታል፤ የገዥው ፓርቲ አባልና ደጋፊ ካልሆነ በስተቀር በዜግነቱ የስራ እድል ማግኘትም ሆነ በነጻነትና በእኩልነት ነግዶ የመኖር እድል ተነፍጎታል፡፡

በአገራችን የተከሰተው የመልካም አስተዳደር እጦት እጅግ ጥልቅና ውስብስብ ሲሆን ይህንን ችግር እየፈጠረ ያለው ማንም ውጫዊ ኃይል ሳይሆን ገዥው ፓርቲ ታማኝ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ናቸው ብሎ በዙሪያው ባሰባሰባቸው ሰዎች ነው፡፡ ከእነዚህ የአገሪቱን ቢሮክራሲ ከቀበሌ እስከ ፌዴራል መንግስቱ መዋቅር ከተቆጣጠሩት የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ውስጥ የችግሩ ተባባሪ ያልሆኑት ሰዎች ቁጥር ከ 4 ወይም ከ 5% ሊበልጥ ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ቁልፍ ጥያቄ እነዚህ ከ 4 እና ከ 5% የማይበልጡ ጨዋ ሰዎች እንዴት አድርገው ከ 96% በላይ የሆነውን የችግሩ ፈጻሚ ኃይል ታግለው ሊያሸንፉት ይችላሉ? የሚል ይሆናል፡፡ ይህ ሃይል በቁጥር ብዙ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን እርስ-በእርሱ በጥቅም የተሳሰረ፣ የመንግስትን የመዋቅር ማሻሻያ ጥረቶች ሁሉ እያመከነ የማስቀረት ልምድ የተካነና መንግስትን መፍራትና መታዘዝ ያቆመ ሃይል ስለሆነ በቀላሉ ሊሸነፍ የሚችል አይደለም፡፡ ይህንን ሃይል ማሸነፍ የሚቻለው በግምገማ፣ በማስፈራራትና በመቅጣት ሳይሆን የስርዓቱ መዋቅራዊ በሽታ የሆነውን የፖለቲካ ሙስና ከሰንኮፉ ነቅሎ በመጣል ነው፡፡

እርግጥ ነው የፖለቲካ ሙስና ሰንኮፍ ከአገራችን ከተነቀለ ኢህአዴግም ከስልጣን የመነቀሉ እድል ሰፊ ይሆናል፡፡ ዞሮ ዞሮ የፖለቲካ ሙስና እስካለ ድረስ ከስልጣን የመነቀሉ ጉዳይ በሌላ መንገድም የማይቀር በመሆኑ በየትኛው መንገድ መነቀል እንደሚፈልግ ምርጫው የኢህአዴግ ይሆናል፡፡ የህዝብን አደራ ከመወጣት፣ በታሪክ ተመስጋኝ ከመሆንና እንደገናም ተመልሶ ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚኖርን እድል ከማስፋት አኳያ ግን በየትኛው መንገድ ስልጣን ማጣት እንደሚበጅ ማወቅ ለማንም ሰው ግልፅ ይመስለኛል፡፡

ኢህአዴግ ይህንን ችግር ከስረ-መሰረቱ ለመፍታት ከፈለገ- በዙሪያዬ ያሰባሰብኩት ኃይል ለምን በዚህ መጠን ሕዝብን የሚያንገላታና ሙሰኛ ሆነ? ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት፡፡ ኢህአዴግ ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት ከደፈረ

የችግሩን ትክክለኛ መፍትሄ ለማግኘትም አይቸገርም፡፡ በእኔ አመለካከት በኢህአዴግ ዙሪያ የተሰባሰበው ሃይል የዚህ ችግር ሰለባ የሆነው በሌላ ምክንያት ሳይሆን ለመንግስት ስራ የሚመለመለውና የሚቀጠረው በችሎታ፣ በእውቀት፣ በልምድና በስነ-ምግባር መመዘኛ ሳይሆን ለስርአቱ ባለው የፖለቲካ ታማኝነት በመሆኑ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ቢያንስ ከቀበሌ እስከ ክልል ባለው መዋቅር የመንግስት ሰራተኛ እየሆነ ያለው ሰው ለኢህአዴግ ዓላማና ፕሮግራም ፍቅር ኖሮት፣ ወይም ህብረተሰብን የማገልገል ፍላጎት ኖሮት፣ ወይም ለኑሮው በቂ ደመወዝና ጥቅም ስለሚያገኝ አይደለም፡፡ እውነቱን በግልጽ መነጋገር ካለብን በአሁኑ ጊዜ የመንግስት ሰራተኛ እየሆነ ያለው አብዛኛው ሰው በደመወዙ ሳይሆን በሙስና ኑሮውን እየደጎመ ለመኖር የሚፈልግ፣ ወይም የተሻለ አማራጭ እስከሚያገኝ ለጊዜው መቆያ የሚሆን ስራ የሚፈልግ፣ ወይም ከመንግስት ስራ ውጭ የመቀጠር እድል የሌለውና በትምህርት ደረጃውና በስራ ብቃቱ ደካማ የሆነ ሰው ነው፡፡

በገጠር አካባቢም በአብዛኛው የኢህአዴግ ካድሬ እየሆነ የሚገኘው ወጣት እርሻና ትምህርት ጠል የሆነው ሲሆን አብዛኛውን የኢህአዴግ የአመራርነት ቦታ የያዙት ደግሞ ኑሮአቸውን ለማሻሻልና ለማደግ ሌላ የህይወት መንጠላጠያ መሰላል ያጡ የገጠር መምህራን ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ ከ 97 ምርጫ በኋላ በሰልፍ የኢህአዴግን መዋቅር የተቀላቀሉት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች በቅንጅት ዙሪያ ሆነው ስርአቱን አምርረው ሲታገሉ የነበሩና ኋላ ላይ በተቃዋሚው ጎራ መፈረካከስ ተስፋ ቆርጠው የድርሻቸውን እየተቀራመቱ ለመኖር ያለ እምነታቸው ስርአቱን የተቀላቀሉ ናቸው፡፡ እንግዲህ ኢህአዴግ በዚህ መልክ በሰበሰበው አድርባይና ጥቅም ፈላጊ ካድሬ አማካኝነት ነው የህዝቡን ነባራዊ ሁኔታ የሚመለከት መረጃ ሰብስቦ፣ በተሰበሰበው መረጃ መሰረትም ፖሊሲና ህገ አውጥቶ አገርን እያስተዳደረ የሚገኘው፡፡ ኢህአዴግ ከፖለቲካ ሙስና ጋር በተያያዘ የገባበትን እንዲህ አይነቱን መጠነ ሰፊ ችግር ጠራርጎ የሚያስወግድ ደፋር እርምጃ ካልወሰደ ችግሩን ከምንጩ ሊያደርቅ አይችልም፡፡

በአጭሩ የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት ብዙ ፍልስፍናና ረቂቅ ምርምር የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ ዋናው መፍትሄ የፖለቲካ ሙስናን ጠራርጎ ማስወገድና መብቱን ተነጥቆ በካድሬዎች ጫማ ስር የወደቀውን ህዝብ መብት ማክበርና እውነተኛ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ህዝብ እውነተኛ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ሆኖ ሹማምንቱን ለስልጣን የመምረጥና ከስልጣን የማውረድ ጉልበት ካለው የመልካም አስተዳደር እጦት መሰረታዊ ምንጭ በዘላቂነት ይደርቃል፡፡ ወሳኙና ዋናው መፍትሄ እንዲህ ዓይነት ቆራጥ የፖለቲካ እርምጃ መውሰድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ- በዚህ አገር የመንግስት ሰራተኛ ሆነው የሚቀጠሩ ሰዎች ለኑሯቸው የሚመጥን ደመዎዝና ጥቅማ-ጥቅምም ሆነ ማህበራዊ ክብር እንዲያገኙ የሚያስችል እርምጃ መውሰድም የመፍትሄው አካል ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡

## **2.4.** የፖለቲካ ምህዳር መጥበብና የአስተሳሰብ ብዙሃነት አለመከበር

ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ ከመምጣትም በላይ እየተዳፈነ መምጣቱ ቢያንስ ከምርጫ 97 በኋላ ሊያከራክር በማይችል ሁኔታ የተረጋገጠ ቢሆንም እንደሌሎቹ ትችቶች ሁሉ ኢህአዴግ በዚህ ረገድ የሚቀርበውን ትችትም ተቀብሎ አያውቅም፡፡ ኢህአዴግ በ 2002 ምርጫ 99.6% ፣ ይባስ ብሎ በ 2007 ምርጫ 100% ምርጫውን አሸንፍኩ ካለ በኋላም ከአፈርኩ አይመልሰኝ ብሎ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ምህዳሩ እየሰፋ ነው በማለት መከራከሩን አላቆመም፡፡ ኢህአዴግ በተለመደ ድርቅናው እንዲህ አይነቱን የምርጫ ውጤት የመድብለ ፓርቲ ስርዓታችን ወደ አውራ-ፓርቲ ዲሞክራሲ መሸጋገሩን የሚያሳይ ነው በማለት በሚያሳፍር ሁኔታ ሊያሳምነን ሞክሯል፡፡

በእኔ በኩል ኢህአዴግ ዘግይቶም ቢሆን በሂደት ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደትን ሊቀበል ይችላል በሚል የነበረኝ ትንሽ ተስፋ ሙሉ በሙሉ የተሟጠጠው ምርጫውን 100% በማሸነፉ ማፈር ሲገባው በድል አድራጊነት ስሜት ሲመጻደቅ በማዬቴ ነበር፡፡ በእኔ በኩል የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ እየተጣበበ በመምጣት የአስተሳሰብ ብዙሃነት

ሊያስተናገድ የማይችልበት ደረጃ መድረሱን ማረጋገጥ የቻልኩት ሰዎች ሲያወሩ ሰምቼ ወይም የተጻፈ አንብቤ አይደለም፡፡ ለ 24 ዓመታት በሂደቱ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆን ችግሩን በተጨባጭ ለማዬት በመቻሌ ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ኢህአዴግን ለመውቀስና ለመተቸት የምሞክረውም ርካሽ የፖለቲካ ተቀባይነት ለማግኘት ብዬ ሳይሆን ፈጽሞ ልጠራጠረው በማልችል ደረጃ እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው፡፡ ኢህአዴግ የሚሰራቸውን በጎ ነገሮች በድፍረት በመመስከሬና በኢትዮጵያ ምክንያታዊ የፖለቲካ ባህል እንዲፈጠር በመሞከሬ ምን ያህል ዋጋ የከፈልኩ ሰው መሆኔ የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ ኢህአዴግ ከእኔ አይነቱ ሰው የሚሰነዘርን ትችት ትንሽም ቢሆን ለማዳመጥ ካልተግደረደረ የማንን ትችት ለማዳመጥ እንደሚችል አይገባኝም፡፡ እንደ ገደል ማሚቱ የራሱን ጩኸት ብቻ እያዳመጠ እስከመቼ እንደሚቀጥልም አላውቅም፡፡ ዞሮ ዞሮ ግማሽ ዕድሜዬን ባሳለፍኩበት የፖለቲካ ተሳትፎ በርግጠኛነት ለመረዳት እንደቻልኩት ኢህአዴግ መሰረታዊ በሆነ ደረጃ /Fundamentally/ አምባገነናዊና ፀረ- ዲሞክራሲ ድርጅት ነው፡፡

ከወቅቱ የአለም አቀፍ የኃይል አሰላለፍ አኳያ የማያዋጣ ስለሆነበት በድፍረት አይናገረው እንጂ ኢህአዴግ ከነጭራሹም በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲም ሆነ መድብለ-ፓርቲ ያስፈልገዋል ብሎ ከልቡ አያምንም፡፡ ነገር ግን በተቃዋሚው ጎራ ውስጥ ያለነው ሰዎች ብቻ ሳንሆን አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብና አለም አቀፉ ህብረተሰብም ኢህአዴግ አምባገነናዊ ድርጅት መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ ተገንዝቧል፡፡ ኢህአዴግ በአንድ በኩል በግራ ፖለቲካ ባህል ተኮትኩቶ ያደገ የ 1960 ዎቹ ትውልድ አካል በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለ 17 ዓመታት ሽምቅ ተዋጊ ሆኖ በመራራ የማሸነፍና የመሸነፍ ሂደት ማንነቱን የቀረፀ ድርጅት ስለሆነ ስህተትን አምኖ መቀበልና ማረም ሽንፈት መስሎ ታይቶታል፡፡ በእርግጥ የዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ባሕል የዚያ ትውልድ አካል የሆኑት- የሻዕቢያ፣ የኦነግ፣ የኢሰፓ፣ የኢህአፓ ወዘተ... ሁሉ መገለጫ ስለሆነ ኢህአዴግ በሆነ ተዓምር ዴሞክራት እንዲሆን መጠበቅ የዋህነት ይመስለኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ኢህአዴግን አሳዛኝ ትዝብት ላይ የሚጥለው አምባገነን መሆኑ ሳይሆን ጧት ማታ አታካች በሆነ መጠን በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ዴሞክራት ነኝ ብሎ ህዝብን ሊያሳምን መሞከሩ ነው፡፡

ኢህአዴግ በ 17 ዓመቱ የትጥቅ ትግል ለከፈለው ከፍተኛ መስዋዕትነት አድናቆትና ክብር የሚገባው ድርጅት ቢሆንም በ 10 ሺዎች በሚቆጠሩ ሰማዕታት ጓዶቹ ስም ጧት ማታ እየማለና እየተገዘተ በአፈናና በሸፍጥ ፖለቲካ ራሱን ዘለዓለማዊ የስልጣን ባለቤት ለማድረግ መሞከሩ ግን ከጊዜያዊ ስልጣን በላይ ለዘላቂ ህልውናውና ታሪኩ የማይጨነቅ ግብዝ ድርጅት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ኢህአዴግ አመነም-አላመነም በገሃድ የሚታየው የአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ የአስተሳሰብ ብዙሃነት ቦታ ማጣቱን በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ የብሄር፣ የሃይማኖትና የባህል ብዙሃነት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ታሪካዊና ወቅታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎች የተፈጠረ በርካታ የአስተሳሰብ ብዙሃነት ባለበት አገር ውስጥ ከቀበሌ እስከ ፌደራል ፓርላማ ድረስ ባሉ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ የሕዝብ ምክር ቤቶች መቀመጫዎች ውስጥ አንድም የሕግ አውጭነት ውክልና ያለው የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የለም፡፡ ከ 70 በላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ በሚባልበት አገር ከቀበሌ ካቢኔ ጀምሮ እስከ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ድረስ አንድም የሕግ አስፈጻሚው አካል የሆነ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የለም፡፡ ህገ-መንግስት ተርጓሚ በሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤትም ሆነ በፍትህ አካሉ ውስጥ የተወከለ አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የለም፡፡

ኢህአዴግ እነዚህን ሶስት የመንግስት ምሰሶዎች በብቸኛነት ሙሉ በሙሉ መቆጣጠሩ አልበቃው ብሎ መንግስታዊ ያልሆኑ የሕዝብ ማህበራትንና የሃይማኖት ድርጅቶችን ሳይቀር በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ በቁጥጥር ስር አውሏቸዋል፡፡ ይህም አልበቃው ብሎ በተቃዋሚነት የተደራጁ ፓርቲዎች ውስጥ ሳይቀር አባላቱን አስርጎ እያስገባ የማዳከምና የመበተን ተግባር ይፈፅማል፡፡ ኢህአዴግ የአገሪቱን አጠቃላይ የፖለቲካ ህይወት በዚህ መጠን ለመቆጣጠር ሲል በፖለቲካ ተቀናቃኞች ላይ

ከፍተኛ ሊባል የሚችል የመብት ረገጣ ይፈፅማል፡፡ ሆኖም ግን አንድም ቀን፣ በአገራችን አንድም የገዥው ፓርቲ አባል በፖለቲካ የመብት ጥሰት ተከሶ ወይም ተቀጥቶ አያውቅም፡፡

ስርዓቱ ሕዝቡ በገሃድ የሚያውቀውን ይህንን እውነት ሽምጥጦ አድርጎ በመካድ አገሪቱ ዴሞክራሲና መድብለ ፓርቲ የሰፈነባት አገር እንደሆነች አድርጎ ሲናገር ስለሚውል በአሁኑ ወቅት መንግስት በተጋነነና በተዛባ ሁኔታ የሚያቀርበውን መረጃ ብቻ ሳይሆን በሃቅም የሚናገራቸውን መረጃዎች ህዝቡ አምኖ መቀበል የማይችልበት ደረጃ ደርሷል፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ድሃው ህዝብ ሳይቀር ሳተላይት ዲሽ በየደሳሳ ቤቱ ጣራ ላይ ሰቅሎ ስለ አገሩ እውነታ መረጃ ለማግኘት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚተላለፉ መገናኛ ብዙሃንን ሲያዳምጥ የሚውለው፡፡ ለአንድ ሕዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ መሆን ከዚህ በላይ ማሳያ ያለ አይመስለኝም፡፡

በአጠቃላይ ኢህአዴግ በሰማዕታቱ ስም እየማለና እየተገዘተ የምታገለው ለዲሞክራሲ ነው ቢልም እየገዛን ያለው ግን በግራ ፖለቲካና በሽምቅ ውጊያ አስተሳሰብ /mind-set/ ነው፡፡ ስለማዳመጥና ስለማሳተፍ ሳይሆን የራሱን አመለካከት በተፅዕኖ ስለማስረጽ፣ ስለመደራደርና መቻቻል ሳይሆን ስለመቆጣጠርና ማሸነፍ እያሰበ የሚሰራ ዴሞክራሲያዊ ባህሪና ባህል የሌለው ድርጅት ነው፡፡ ኢህአዴግ አንዳንድ ጊዜ ሲናገሩ እንደምንሰማውም የተቃዋሚ ፓርቲዎችን መኖር የሚፈልጉት ጥፋቱን እየተናገሩ ስህተቱን የማረም ዕድል እንዲሰጡት ነው እንጂ እውነተኛ የፖለቲካ ስልጣን ተቀናቃኝ እንዲሆኑ አይደለም፡፡

የወቅቱ የሕዝብ ዓመጽ በአጋጣሚና በስሜት የተፈጠረ ሳይሆን ኢህአዴግ ከስረ-መሰረቱ አምባገነናዊ ድርጅት መሆኑን ከመረዳትና እንዲህ አይነቱን ድርጅት በትግልና በመስዋዕትነት እንጂ በጥያቄና በተማፅኖ መቀየር እንደማይቻል ህዝቡ ከልቡ ስለተረዳ ነው፡፡ በተገቢው ጊዜና መንገድ እራሱን ማደስ የማይችል ማንኛውም አምባገነናዊ ስርአት በመጨረሻ ሊያስተናግድ የሚችለው አብዮትና የትጥቅ ትግልን ስለሆነ ኢህአዴግም ዛሬ ላይ የገጠመው ችግር ዕድለ-ቢስ ስለሆነ ወይም ህዝቡ ውለታ-ቢስና ክፉ ስለሆነ ሳይሆን የዘሩትን ማጨድ አይቀሬ ስለሆነ ነው፡፡

ኢህአዴግ ከማንም በላይ ስለ ሰላምና መረጋጋት አስፈላጊነት ሲሰብክ የኖረ ድርጅት ቢሆንም በተግባር ግን ከህዝብ ልብ ውስጥ ሰላምን የሚያርቅና የሚያጠፋ ድርጊት ሲፈጽም የሚውል ድርጅት ነው፡፡ ስልጣን ላይ በወጣ በጥቂት አመታት ውስጥ ራሱ ወደ ትጥቅ ትግል ለመግባት የተገደደበትንም ሆነ ለስልጣን የበቃበትን ምክንያት ረስቶ ያሸነፈውን መንግስት ታሪክ እየደገመ ያለ ድርጅት ነው፡፡

በአጠቃላይ ሕዝቡ በፓርቲዎች ዙሪያ በአግባቡ ተደራጅቶ በመታገል ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት ባይችልም እንኳ ብሶቱ፣ ምሬቱና ተቃውሞው የሚደመጥበት መድረክ እንዲኖረው ይፈልጋል፡፡ ከ 2002 ምርጫ በኋላ ግን የሕዝቡን አመለካከት የሚወክሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ህዝባዊ ማህበራት በስርዓቱ የአፋኝነት ድርጊት ከሂደቱ ተጠራርገው እንዲወጡ በመደረጋቸው ሕዝቡ በአመፅና በነውጥ የታፈነ ስሜቱን ለመግለጽ ተገዷል፡፡ ስርዓቱ በሚፈፅመው የአፈና ተግባር ምክንያት በሰላማዊና ህጋዊ ትግል አዋጭነት ላይ ህዝቡ ያለው ተስፋ ተሟጦ በመጥፋቱም የወቅቱን የህዝብ ትግል የመምራቱን ዕድል በስደት የሚገኙ አክራሪ የፖለቲካ ሃይሎች ወስደውታል፡፡

የአገሪቱን የፖለቲካ ዕውነታ በገለልተኝነትና በድፍረት የሚያወራ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንዳይኖር በመደረጉም የህዝቡን ጀሮና ቀልብ የሚስቡት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚሰራጩት አመጽና ጦርነት ቀስቃሽ ሚዲያዎች ሆነዋል፡፡ ይህ ዕውነታ ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ የወቅቱ የህዝብ ትግል የሚመራው አገር ውስጥ ከህዝቡ ጋር አብረው እየኖሩ ባሉ ህጋዊና ሰላማዊ ፓርቲዎች እንዲሆን ካልተደረገና በህዝቡ የሚደመጡትና የሚታመኑት እዚሁ አገር ውስጥ የሚገኙት መገናኛ ብዙሃን እንዲሆኑ ካልተደረገ በስተቀር የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ መቼውንም ግዜ ቢሆን ጤናማና ሰላማዊ ሊሆን አይችልም፡፡ ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት ሊቋቋመው ባልቻለ የፖለቲካ ነውጥ እየታመሰ የሚገኘው እንዲሁ ዕድለ-ቢስ ድርጅት ስለሆነ ሳይሆን አገር ውስጥ

የሚገኙ ፓርቲዎችና ሚዲያዎች እንዲዳከሙ ሆን ብሎ በሰራው ስህተት ምክንያት ነው፡፡ የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር አሁን ከሚገኝበት እንደሌለ ከሚያስቆጥር ሁኔታ በከፍተኛ መጠን እንዲሰፋ ካልተደረገና የአስተሳሰብ ብዙሃነት የሚስተናገድበት ተጨባጭ ለውጥ በፍጥነት ካልመጣ የወቅት የአገራችን የፖለቲካ ቀውስ የበለጠ እየተባባሰ እንጂ ከቶውንም እየረገበ ሊመጣ አይችልም፡፡

## 2.5. የሕውሃት የበላይነት

ኢህአዴግ ለስልጣን ከበቃበት ጊዜ ጀምሮ የሕውሃት የበላይነት ጉዳይ ሕዝቡ ስርአቱን ለሁሉም ህዝብ እኩልነትና የጋራ ተጠቃሚነት የቆመ ፍትሃዊ ስርአት አድርጎ እንዳያየው በማድረግ ረገድ በቁጥር አንድ ሊጠቀስ የሚችል ችግር ነው ቢባል ማጋነን አይመስለኝም፡፡ ከኢህአዴግ ታሪካዊ አመጣጥ ለመረዳት እንደምንችለው በ 17 ዓመቱ የትጥቅ ትግል ህውሃት የትጥቅ ትግሉን ቀድሞ በመጀመር ፣ በርካታ ተዋጊ ኃይል በዙሪያው በማሰባሰብና ከፍተኛውን የመስዋዕትነት ዋጋ በመክፈል ረገድ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ ድርጅት ነው፡፡ ከደርግ ጋር የተካሄደውን የትጥቅ ትግል በአሸናፊነት ለመወጣት የሚያስችል ወታደራዊና ፖለቲካዊ ሀሳቦችን በማፍለቅና ድርጅታዊ አመራር በመስጠት ረገድም ቁልፍ ሚና የተጫወተ ድርጅት ነው፡፡ በዚህ ታሪካዊ ሚናው ምክንያት ህውሃት በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የሀይል አሰላለፍ ውስጥ የበላይነት ያለው ድርጅት ብቻ ሳይሆን የአባል ድርጅቶቹ ፈጣሪም ለመሆን በቅቷል፡፡

የቀድሞ ኢህዴን አፈጣጠር አከራካሪ ቢሆንም ቀደም ሲል ኢህዴን የኢህአዴግ መስራች አባል እንዲሆን በማድረግ እና በኋላም ላይ ኢህዴን ወደ ብአዴንነት ተቀይሮ የአማራው ሕዝብ ገዥ እንዲሆን በማድረግ፤ ኦህዴድንና ደህዴንንም በመልክ በመልክ አደራጅቶ በመፍጠር ለኦሮሚያና ለደቡብ ሕዝቦች ገዥ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ህውሃት መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ ይህ ህውሃት በትጥቅ ትግሉ ወቅትና በኢህአዴግ የመንግስት ምስረታ ወቅት የነበረው ሁለንተናዊ የበላይነት በሂደት መለስተኛ ለውጥ እየታየበት የመጣ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ሳይቋረጥ ቀጥሏል፡፡

የህውሃት የበላይነት ጉዳይ በአንድ በኩል ሕዝቡ ስርአቱን ከጅምሩ ፍትሃዊ የሆነ የጋራ ስርአት አድርጎ እንዳያየው የራሱን አሉታዊ አስተዋጽኦ ያበረከተ ሲሆን ፤ ከዚያ በላይ ግን ጽንፈኛ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች በስርዓቱ ላይ አንድ ጠንካራ ተቃውሞ የመቀስቀሻና የማነሳሻ አጀንዳ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ በዚህ የህውሃት የበላይነት ምክንያት አብዛኛው ህዝብ ስርዓቱን የወያኔ፣ ከዚያም አለፍ ሲል የትግሬ ስርዓት አድርጎ እንዲመለተከው፤ ከዚህ በተቃራኒም ከህውሃት ውጭ ያሉትን የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንደ አሻንጉሊት በመቁጠር በንቀት እንዲመለከታቸውና ተገቢ እውቅና /legitimacy/ እንዳይሰጣቸው አድርጓል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ይህ በኢህአዴግ ውስጥ ያለ የሕውሃት የበላይነት አክራሪ የፖለቲካ ሀይሎች ከሚያካሂዱት ቅስቀሳ ጋር ተደምሮ ሕዝቡ ያለአግባብ ሕውሃትንና የትግራይን ሕዝብ ነጣጥሎ ማዬት እንዳይችልና በትግራይ ሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ ላይ የተዛባና ጤናማ ያልሆነ አመለካከት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ ይህ ሁኔታም በአገራችን ያለውን የፖለቲካ ቅራኔ የአስተሳሰብ ቅራኔ ከመሆን አልፎ ወደ ዘረኝነት የተጠጋ ቅራኔ እንዲሆን በማድረግ አስቀያሚ ገፅታ እንዲላበስ አድርጎታል፡፡

የሕውሃትን የበላይነት በሶስት መልክ ከፍለን ልናዬው እንችላለን፡፡ አንደኛ ቀደም ሲል በህገ-መንግስቱ ውስጥ ስላሉ አንዳንድ ድንጋጌዎች ለመግለጽ እንደሞከርኩት ህውሃት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ራሱን የበላይ አድርጎ ምን ያህል እንደሚቀጥል እርግጠኛ ባለመሆን በውስጡ የነበረውን ስጋትና ጥርጣሬ ለመግለጽ የሞከረው ለራሱ የሚጠቅሙ ህጎችን በመደንገግ ብቻ ሳይሆን ከስልጣን የበላይነት ጋር ወሳኝ ቁርኝት ያላቸውን የመንግስት የሃላፊነት ቦታዎች በመቆጣጠር ጭምር ነበር፡፡ በአገሪቱ የመንግስት መዋቅር በቅደም ተከተል ወሳኝ የሚባሉትን አራት ቦታዎች ማለትም የጠቅላይ ሚኒስትርነት፣ የኢታማጆር ሹምነት፣ የአገር ውስጥ ደህንነት ኃላፊነትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነትን ስልጣን በብቸኝነት ተቆጣጥሯቸው ኖሯል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በሞት እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ እነዚህ ቁልፍ የመንግስት የስልጣን ቦታዎች ያለ ይሉኝታና የብሄረሰብ ተዋጽኦ ኮታ ሳይመለከታቸው በህውሃት ብቸኛ ቁጥጥር ስር ሆነው የኖሩ ናቸው። ከእነዚህ ቁልፍ ኃላፊነቶች በተጨማሪም ለአንድ መንግስት የስልጣን የበላይነትና ደህንነት ወሳኝነት ባላቸው መከላከያን፣ ደህንነትን፣ ኢሚግሬሽንን፣ ስደተኞች ጉዳይን፣ ፌዴራል ፖሊስን፣ ማረሚያ ቤቶችን፣ ጉምሩክን፣ አቬሽንንና አየር መንገድን በመሳሰሉ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ወሳኝ የሚባሉትን ሃላፊነቶች በጎላ ሁኔታ ተቆጣጥረው የኖሩትና አሁንም የሚኖሩት የህውሃት አባላት ወይም ለህውሃት ታማኝነት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ከእነዚህ ውጭ ባሉ የፌዴራል የመንግስት መስሪያ ቤቶችም ሚስጥር ነክ መረጃ ያላቸውና ለሙስና ተጋላጭ ናቸው ተብለው የሚሰጡ ኃላፊነቶች በጥንቃቄ ተመርጠው በህውሃት ሰዎች እንዲያዙ ይደረጋሉ።

ይህንን እውነታ ህዝቡ የሚያስፈጽመው ጉዳይ ኖሮት ወደ እነዚህ መስሪያ ቤቶች ሲሄድ በሚያየው ሁኔታና ከአክራሪ የፖለቲካ ኃይሎች በሚሰማው ቅስቀሳ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ለቃለ መጠየቅ የሚቀርቡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ሃላፊዎችን ቤቱ ውስጥ ቁጭ ብሎ ሲመለከት በስማቸውና በድምፅ ቅላጼያቸው በቀላሉ ለይቶ እየቆጠረ እውነታውን ይረዳዋል። ከሕዝቡም በላይ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ደፍረው በመድረክ ባይናገሩትም እውነታውን በቅርበት ጠንቅቀው ያውቁታል። የእነዚህ ድርጅቶች አባላት በተለያዩ ምክንያቶች ከድርጅታቸው ተነጥለው ሲወጡ የሕውሃትን የባላይነት በዋና የተቃውሞና የብሶት መግለጫነት ሲጠቀሙበት አይተናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ይህ ጉዳይ አንዳንድ የኦህዴድና የብአዴን ካድሬዎች ከህውሃት እይታ ተሰውረው ህዝቡን በመንግስት ላይ የሚያነሳሱበት አጀንዳ እንደሆነና በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የውስጥ ግምገማ ላይም የመወያያ ርዕስ እየሆነ እንደመጣ እየሰማን ነው።

ሁለተኛው የሕውሃት የበላይነት መገለጫ ስነ-ልቦናዊ የበላይነት ነው። ከማንም በላይ የሕውሃት አባላት እራሳቸውን የስርአቱ ባለቤትና ጠባቂ አድርገው ስለሚያስቡ ተጨባጭ የስልጣን ቦታ ኖራቸውም አልኖራቸውም በዩ መስሪያ ቤቱ የሁሉም ነገር አድራጊና ፈጣሪ መስለው የሚታዩት እነሱ ናቸው። በአንድ መስሪያ ቤት ውስጥ ያላቸው የስራ ድርሻ ተላላኪነት ፣ ጥበቃ ወይም ጽዳት ሰራተኝነት ቢሆንም እንኳ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ለስርአቱ ተቆርቋሪነት የሚያሳዩትም ሆነ ተበድያለሁ ለሚል ባለጉዳይ አማላጅ ሆነው ለመቅረብ የሚሞክሩት የህውሃት ሰዎች ናቸው።

እንዲህ አይነቱ የስነ-ልቦና የበላይነት በመንግስት መስሪያ ቤቶች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሕዝቡ ማህበራዊ ኑሮዎች ጭምር የሚታይ ነው። በየታክሲው ውስጥ፣ በየመጠጥ ቤቱ፣ በየዕድሩ፣ በየቀበሌው ወዘተ … ከማንም በላይ እራሳቸውን የስርአቱ ባለቤትና ጠበቃ አድርገው በማየት ስለ ሰላምና ልማት አስፈላጊነት ሕብረተሰቡን ለማስተማር ሲሞክሩ የሚታዩት እነሱ ናቸው። የልማት መዋጮ ሲሰባሰብ ቀድመው የሰው ቤት የሚያንኳኩት፤ ሕገ-ወጥ ግንባታ ተካሄደ ሲባል ቀድመው ለቀበሌ ጠቋሚ የሚሆኑት፣ በየቀበሌው በሚካሄዱ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በአስተናጋጅነት ቀድመው ሽር-ጉድ የሚሉትና በስብሰባው ላይ የሁሉም ነገር ተንታኝ ሆነው የሚቀርቡት የህውሃት አባላት ናቸው። ይህ ሥነ-ልቦናዊ የበላይነት ቀስ-በቀስ ከማንም በላይ አገር ወዳዶች፣ ጀግኖችና አዋቂዎች እኛ ነን ወደሚል የትምክተኝነት ባህሪ እየተቀየረ መጥቷል። ይህ በአብዛኛው በመሃል አገር በሚገኙ ጥቂት የሕውሃት አባላት የሚንጸባረቀው የትምክህት ባህሪ በሚሊዮን የሚቆጠረውን ትሁትና ጨዋ የሆነውን የትግራይ ሕዝብ በቅርበት ማዬት እድል ላላገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተዛባ ዕይታ /perecepion/ በመፍጠር በአገሪቱ አጠቃላይ ፖለቲካ ላይ አሉታዊ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ሶስተኛው የሕውሃት የበላይነት ከኢኮኖሚ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችል ነው። ማንኛውም የፖለቲካ ስልጣን የበላይነት ያለ ኢኮኖሚያዊ የበላይነት ራሱን ችሎ ሊቆም እንደማይችል ህውሃት ጠንቅቆ የሚያውቅ ድርጅት ነው። ሕውሃት ከዚህ ዕምነቱ በመነጨ ከአገሪቱ የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ሂደት በተቃራኒ ራሱን የበርካታ በቢሊዮን የሚቆጠር በጀት የሚያንቀሳቅሱ የንግድ ድርጅቶች ባለቤት አድርጓል። ተመሳሳይ የንግድ ተቋማት በማቋቋም ረገድ ለይስሙላ ያህል ሌሎቹም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንዲሳተፉ የተደረገ ቢሆንም በህውሃትና በሌሎቹ ድርጅቶች የንግድ ተቋማት መካከል ያለው የአቅም ልዩነት ግን

ፈጽሞ ሊነጻጸር የሚችል አይደለም፡፡ ሶስቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንወክለዋለን በሚሉት የሕዝብ መጠን ከአስር እጥፍ በላይ ከህውሃት የሚበልጡ ቢሆኑም የሶስቱ ድርጅቶች የንግድ ተቋማት አቅም ተደምሮ የሕውሃትን አንድ ሶስተኛ አያክልም፡፡

እነዚህ የህውሃት የንግድ ድርጅቶች የአገሪቱን ህግ በተዘዋዋሪ መንገድ ጥሰው የተቋቋሙት የትግራይ ክልልን ለማልማትና የህውሃትን የፖለቲካ የበላይነት አስጠብቆ ለማስቀጠል ታስቦ ነው ቢባልም የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከት መፈልፈያ በመሆን ስርአቱን ለአደጋ አጋለጡት እንጂ እንደታሰበው ለትግራይ ክልልም ሆነ ለራሱ ለሕውሃት የሚጠቅሙ አልሆኑም፡፡ በአንድ አገር ፓርቲና የንግድ ስራ ሲደባለቁ ምን አይነት አደጋ እንደሚያስከትል በሰሞኑ የአገራችን የፖለቲካ ብጥብጥ በሰላም ባስ፣ በዳሽን ቢራና በአባይ ባንክ ላይ ከደረሰው ጉዳት በቀላሉ ለመረዳት እንችላለን፡፡

ኢህአዴግ እንዲህ አይነቱ መዋቅራዊ ሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ጠቃሚ እንዳልሆነ ተረድቶ ችግሩን ማረም ሲገባው ይባስ ብሎ የአገሪቱን መከላከያ ሰራዊት ወደ መጠነ ሰፊ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በማስገባት ችግሩን ይበልጥ እንዲባባስና ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ በአብዛኛው ቁልፍ የኃላፊነት ድርሻ ያላቸው የቀድሞ የሕውሃት አባላት ስለሆኑ ከሰራዊቱ አመራሮች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው የሕውሃት አባላትና ደጋፊዎች የኪራይ ሰብሳቢነት ሰለባ መሆናቸውን ይበልጥ አባብሶታል፡፡

ከህውሃት የኢኮኖሚ የበላይነት ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚችለው ሌላው ችግር አብዛኛዎቹ የትግራይ ተወላጆች እንደማንኛውም ዜጋ በሃቅ ጥረው ግረው ሃብት ለማካባት የበቁ ቢሆንም፣ ከስርአቱ ጋር ባላቸው ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር ያለ አግባብ ተጠቃሚ በመሆን በጥቂት አመታት ውስጥ ጉምቱ ባለሀብት ለመሆን የበቁ በቁጥር አናሳ፣ ነገር ግን የዕይታ ትኩረትን የሚስቡ የትግራይ ተወላጆች የመኖራቸው ጉዳይ ነው፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት የከባድ መኪና ሾፌር፣ የመከላከያ ሰራዊት አባል ወይም የመንግስት ሰራተኛ የነበሩ ሰዎች የገንዘብ ምንጫቸው በግልጽ ባልታወቀ ሁኔታ በሚሊዮን ብር የሚቆጠር በጀት የሚያንቀሳቅስ ድርጅት ባለቤት ሲሆኑ ይታያል፡፡ እነዚህ በኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡ ሰዎች ለወታደራዊና ሲቪል ባለስልጣናት የተመሩ መሬቶችን በመግዛት፣ ለሊዝ ጨረታ የወጡ ቁልፍ ቁልፍ መሬቶችን ተሻምቶ በመግዛት በአዲስ አበባ አንዳንድ አካባቢዎች የነሱ ቋንቋ ጎልቶ የሚነገርበት መንደርና ጎዳና እስከመፍጠር ደርሰዋል፡፡ በዚህ አይነት አካሄድ ለመክበር የበቁ ሰዎች ከሁሉም ብሄረሰብ ሊገኙ ቢችሉም ከፍሲል ከዘረዘርኳቸው የፖለቲካ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የበለጠ ጎልተው የሚታዩትና ትኩረት የሚስቡት ግን ትግርኛ ተናጋሪዎቹ ሆነዋል፡፡

እነዚህ ያለ አግባብ ለመክበር የበቁ ሰዎች ከአጠቃላዩ የትግራይ ህዝብ ቁጥር ጋር ሲነፃፃሩ በቁጥር ጥቂት ሊባሉ የሚችሉ ቢሆኑም "የትግራይ ህዝብ ልዩ ተጠቃሚ ሆኗል" በማለት ለሚቀሰቅሱ ፅንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች ግን ጥሩ አጀንዳ ሆኖ አገልግሏቸዋል፡፡ በሚሊዬን የሚቆጠረው የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለዬ የተጠቀመው ነገር ባይኖርም በእነዚህ በባህሪም ሆነ በኑሮ ደረጃቸው የትግራይን ህዝብ በማይመስሉ ጥቂት ባለሃብቶች ምክንያት የትግራይ ህዝብ ለከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ተጋልጧል፡፡

በቅርቡ በአገራችን በታዬው የፖለቲካ ቀውስም የትግራይ ተወላጆች የፕሮፓጋንዳ ብቻ ሳይሆን የቀጥተኛ ጥቃት ሰለባ ሲሆኑ ታይተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ወደዚህ አስቀያሚ ደረጃ የደረሰው በአንድ በኩል የትግራይ ህዝብንና ህውሃትን፣ በሃቅ ለፍቶና ደክሞ ባለሃብት የሆነውን የትግራይ ተወላጅና ከስርአቱ ጋር ተመሳጥሮ በአቋራጭ የከበረውን የትግራይ ባለሃብት አንድና አንድ አድርገው በሚያዩ ፅንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች ቅስቀሳ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ መንግስት ከህውሃት የበላይነት ጋር በተያያዘ በአግባቡ ከህዝብ እየተነሱ ላሉ ቅሬታዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት ባለመቻሉ ነው፡፡

ወደፊትም ይህ ከህውሃት የበላይነት ጋር በተያያዘ የሚቀርበው የህዝብ ቅሬታ በአግባቡ ዕውቅና አግኝቶ ካልታረመ በስተቀር የተገቢ ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን የአክራሪነት የመቀስቀሻ መሣሪያ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው፡፡ በአገሪቱ እየታዬ ያለውን የወቅቱን የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግርም የበለጠ ያባብሰዋል፡፡ እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት አንድ ቁም ነገር ከህውሃት የበላይነት ጋር በተያያዘ በተፈጠረው የፖለቲካ ችግር ምክንያት ከማንም በላይ ጉዳት እየደረሰበት የሚገኘው የትግራይ ህዝብ በመሆኑ ይህንን ፍትሃዊ ያልሆነ የህውሃት የበላይነት የትግራይ ህዝብ ከማንም ባላነሰ መቃወምና መታገል ይኖርበታል፡፡ የትግራይ ህዝብ ከእንግዲህ ያለፈው ስርዓት ተመልሶ ይመጣብሃል በሚል ማስፈራሪያና በ 17 ዓመቱ የትጥቅ ትግል ሰማዕታት ስም እየተገዘተ የህውሃት የአስተሳሰብ እስረኛ መሆን የለበትም፡፡ አግባብ ባለው መልኩ የህዝቡን ህጋዊና ሰላማዊ ትግል በመቀላቀል የአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች ምንጭ ተደርጎ ከመታየት ወደ የአገሪቱ የፖለቲካ የመፍትሄ አካልነት መሸጋገር አለበት፡፡ በተለይም አዲሱ የትግራይ ትውልድ ህውሃትን ብቸኛ የትግራይ ህዝብ ወኪል አድርጎ የማምለክን አስተሳሰብ ሰብሮ በመውጣት ከራሱና ከጊዜው ዘመናዊ አስተሳሰብ የሚመጥን የፖለቲካ መስመር መያዝ አለበት፡፡

## 2.6. የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ ህፀፆች

አሁን አሁን የርዕዮተ-ዓለም አቅጣጫ ያጡ አንዳንድ የአፍሪካ መንግስታት የልማታዊ መንግስትን ቀዳሚ ትርጉም ለራሳቸው በሚጥም መንገድ እየቀየሩ ሊጠቀሙበት ቢሞክሩም በአብዛኛው የደቡብ ምስራቅ ኤዥያ አገሮች እንደታየው ¨የልማታዊ መንግስት ዋና መገለጫ ባህሪ - መንግስት ራሱን ዋና የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጎና የፖለቲካ መብቶችን ደፍቆ፣ ጠንካራ ዲሲፒሊን ባለው ቢሮክራሲ አማካኝነት ፈጣን የኢኮኖሚና የልማት እድገትን ማምጣት ነው፡፡ የልማታዊ መንግስት ትክክለኛ መገለጫው ይህ ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያ አስመሳይ (Pseudo) ዴሞክራሲ ያላቸው አንዳንድ አገሮች “ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ነን” በማለት ራሳቸውን በመጥራት ልማታዊ መንግስትነት ዴሞክራሲንም ሆነ የኢኮኖሚ እድገትን በጣምራ ማምጣት የሚያስችል ስርዓት ነው በማለት አዲስ- ግን ትርጉም የለሽ አስተሳሰብ ይዘው መጥተዋል፡፡

ትርጉም የለሽ የሚሆንበት ምክንያት- አንድ መንግስት ዴሞክራሲንና የኢኮኖሚ እድገትን በጣምራ ማምጣት ከቻለ በአብዛኞቹ የምዕራብ ሃገሮች እንደሚታየው የዚያ ዓይነቱ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ ወይም የካፒታሊስት ስርዓት ተብሎ ይጠራል እንጂ በተለዩ ሁኔታ ¨ልማታዊ መንግስት” ተብሎ መጠራት አያስፈልገውም፡፡ ምክንያቱም በ 1970 ዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ ¨ልማታዊ መንግስት” የሚለው መጠሪያ የተፈጠረው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሳይኖራቸው በአምባገነናዊ መንግስት እየተመሩ ትክክለኛ ነው ተብሎ ከታመነበት መንገድ ውጪ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያመጡ ያሉ የደቡብ ምስራቅ ኤዥያ አገሮችን ምን ብለን እንጥራቸው ? ለሚለው የወቅቱ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ተብሎ ቻልመርስ ጆንሰን በተባለ ሰው የወጣ ስያሜ ነው፡፡ አንዳንድ ቦትስዋናን የመሰሉ አንጻራዊ ዴሞክራሲ ያላቸው አገሮች መንግስታቸው በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ ቁጥጥር ያለው ከመሆኑ አንጻር ¨ልማታዊ መንግስት¨ እየተባሉ በተለምዶ ቢጠሩም ይህ መጠሪያ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው ግን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሳይኖራቸው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ላመጡ የኤዥያ አገሮች ነው፡፡ ኢህአዴግም የዛሬ 15 ዓመት ገደማ (በህወሃት መፈረካከስ ወቅት) ርዕዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ አጥቶ ሲውረገረግ በአቶ መለስ ዜናዊ አማካኝነት በድንገት ጠልፎ የያዘው ስያሜ ነው እንጂ ልማታዊ መንግስትነት ከመጀመሪያው በበቂ ጥናትና ትንታኔ ተደግፎ በድርጅት ውሳኔ የተያዘ መስመር አይደለም፡፡

ዞሮ ዞሮ ቀደም ሲል ኢህአዴግ ምን ያህል ፀረ-ዴሞክራሲ ባህሪ ያለው ድርጅት መሆኑን ለማሳየት እንደሞከርኩት እንደ ብዙዎቹ የደቡብ ምስራቅ ኤዥያ አገሮች ኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በመድፈቅ ፈጣን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማምጣት እየሰራ የሚገኝ ድርጅት ነው፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን በያዘበት ወቅት የቀዝቃዛው ጦርነት በምዕራቡ አለም አሸናፊነት የተደመደመበት ወቅት ስለነበረና እሱን ተከትሎ የመጣው የዓለም የሃይል አሰላለፍ የማያመች ሆኖበት እንጂ ኢህአዴግ

በውስጣዊ ዕምነቱ ከቻይና የተለየ አመለካከት ያለው ድርጅት አይደለም፡፡ ኢህአዴግ በየዕለቱ በሚያሰራጨው ፕሮፖጋንዳ ምዕራባውያንን ሲያንቋሽሽ የሚውለው፣ የዜጎችን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ሲያፍን የሚውለው፣ የፓርቲ የንግድ ድርጅት አቋቁሞ የሚነግደው፣ ከካድሬ እስከ ጋዜጠኛና ባለሃብት ያለው ህብረተሰብ በሙሉ ልማታዊ መሆን አለበት ብሎ ጫና የሚፈጥረው በእርግጥም ዴሞክረሲዊ ያልሆነ ቻይናዊ ልማታዊ መንግስት ስለሆነ ነው፡፡ በቻይና ኮሚኒስት ፓርቲና በኢህአዴግ መካከል ያለው መሰረታዊ ልዩነት- የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ያለምንም ማስመሰል በአሁኑ ወቅት ለቻይና ህዝብ የሚያስፈልገው የኢኮኖሚ እድገት እንጂ ዴሞክራሲዊ ስርዓት አይደለም ብሎ በግልጽ ይናገራል፤ ኢህአዴግ ግን በተግባር ላይፈጽመው ኢኮኖሚያዊ እድገትም ሆነ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የሞት የሽረት ጥያቄ ነው እያለ ያስመስላል፡፡

ይህ የኢህአዴግ የተንሻፈፈ አመለካከት ያስከተላቸው ችግሮች (ወረድ ሲል እናያቸዋለን) መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በኢኮኖሚ እድገትና በልማት መስፋፋት ረገድ ኢህአዴግ ባለፉት 20 ዓመታት ያስመዘገበው ውጤት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በተለይም በመሰረተ-ልማትና በትምህርት መስፋፋት ረገድ (የጥራት ጉድለቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) በኢህአዴግ ዘመን የተሰራው ስራ እንደ ትውልድ ሁላችንንም ሊያስደስትና ሊያኮራ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ የኢኮኖሚ እድገትና የልማት መስፋፋት ጉዳይ ከድህነት የመላቀቅና የመበልጸግ ጥያቄ በመሆኑ ለፖለቲካዊ ደህንነታችንም ሆነ ለሃገራችን ህልውና መቀጠል ያለው ፋይዳ ከፍተኛና የማይተካ ነው፡፡ በኢኮኖሚው ዙሪያ የሚታየው እድገት በአንድ በኩል የስራ እድልና የኑሮ መሻሻል ተስፋ በመፍጠር አንጻራዊ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲኖረን ያደረገ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ እየተፈጠረ ያለው የመሰረት ልማት መስፋፋት ህዝቡ ዕርስ-በዕርሱ እንዲተሳሰርና የመሃሉና የዳሩ አገር ህዝብ እንዲቀራረብ በማድረግ አንጻራዊ አንድነት እንዲኖረን አድርጓል፡፡

ላለፉት 25 ዓመታት የአንድነት ሳይሆን የልዩነት ፕሮፖጋንዳ ያለማቋረጥ ሲነዛ የመኖሩን ያህል ተስፋ ሰጭ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት በአገራችን ባይኖር ኖሮ ከእነ ችግሮቹም ቢሆን ዛሬ በአገራችን የሚታየው አንጻራዊ የፖለቲካ መረጋጋትም ሆነ የአገር አንድነት ጭራሹንም ላይኖር ይችል ነበር፡፡ ስለሆነም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ማንም ይሁን ማን፣ እንውደደውም እንጥላውም የኢኮኖሚ ዕድገት ከአጠቃላዩ ህልውናችን ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ቁም ነገር ስለሆነ ለአፍታም ሳይቋረጥ የሞት የሽረት ትግል ተደርጎ መቀጠል አለበት፡፡

የተማረና መካከለኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ በመፍጠር ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥረው፣ ህዝቡን በመሰረተ-ልማት ግንባታ በማስተሳሰርና በማቀራረብ የዳር ሃገሩን መሃል በማድረግ የህዝብና የአገር አንድነትን በከፍተኛ ፍጥነት ማጠናከር የሚችለው ከምንም ነገር በላይ የኢኮኖሚና የልማት እድገት ጉዳይ ስለሆነ በአገሪቱ ያለው ስርዓት አምባገነናዊ በሆነበትም ሁኔታ ሳይቋረጥ መቀጠል ያለበት ነው፡፡ የልማትና የኢኮኖሚ ዕድገት በሂደት መብቱን የመጠየቅና ጥቅሙን የማስከበር አቅም ያለው ጠንካራ ህዝብ በመፍጠር የአምባገነናዊ ስርዓትን ዕድሜ የሚያሳጥር እንጂ አንዳንድ ጽንፈኛ የፖለቲካ ሃይሎች እንደሚሉት የአምባገነኖችን ዕድሜ የሚያራዝም አይደለም፡፡ በአሁኑ ወቅት በህዝብ ትግል ስም ኢንቨስትመንትን በሃገራችን እንዳይስፋፋ የሚደረገውን ቅስቀሳና ንብረትን በማቃጠልና በማውደም እየተካሄደ ያለውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ መቃወም ያለብን ከቅርቡ የኢኮኖሚ ጥቅማችን አንፃር ብቻም ሳይሆን ከሩቁ የፖለቲካ ጥቅማችን ጭምር አንፃር ነው፡፡

ነገር ግን ከልማታዊ መንግስት አመለካከት ጋር በተያያዘ በኢኮኖሚው ዘርፍም ለህዝቡ ብሶት መባባስ ተጨማሪ ምክንያት የሆኑ ችግሮች በአገራችን አሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች እንደሚከተለው እርስ በእርስ ተዛማጅ በሆኑ በሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

### 2.6.1. ከገደብ ያለፈ የኢኮኖሚ ቁጥጥርና ጣልቃ ገብነት

ከፍ ሲል ከአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ኢህአዴግ ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ኢኮኖሚውን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው ከሚለው አመለካከቱ ጋር በተያያዘ በኢኮኖሚው ውስጥ ከፍተኛ ቁጥጥርና ጣልቃ ገብነት ያለው መንግስት ነው፡፡ በፓርቲ ድርጅቶች፣ በመከላከያ ሰራዊቱና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አማካኝነት በከፍተኛ የንግድ ስራ ውስጥ የገባ ከመሆኑም በላይ ሲያስፈልገውም ተራ የሸቀጣ ሸቀጦችን ዋጋ እስከመተመን በሚደርስ ተግባር የኢኮኖሚ ገበያውን ለመቆጣጠር የሚሞክር ድርጅት ነው፡፡ በዚህ የተዛባ አስተሳሰብ ምክንያት በልማት ስራና በስራ ቀጣሪነት ከፍተኛ ሚና ሊጫወት የሚገባው የአገራችን የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚገባውን ያህል ማደግና መስፋፋት አልቻለም፡፡ ከዕዝ ኢኮኖሚ ወጥተን ወደ ገበያ ኢኮኖሚ ገባን ከተባለ 25 ዓመታት የሆነን ቢሆንም በአገራችን ዋናው አልሚና ስራ ቀጣሪ አሁንም መንግስት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በዚህም ምክንያት መንግስትና በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያለው የሰው ሃይል በከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የሙስና ተግባር ውስጥ የተዘፈቀ ሲሆን፣ በተጨማሪም የአገሪቱ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዳይኖረው አድርጓል፡፡

መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ዋና ስራ ቀጣሪ ሆኖ መቀጠሉ ስራ ተቀጣሪነትን ከፓርቲ አባልነትና ደጋፊነት ጋር በማያያዝ የፖለቲካ ሙስና እንዲፈጽም አድርጎታል፡፡ በአሁኑ ወቅት መንግስት በሚፈጥራቸው የስራ እድሎች ወጣቶች ስራ እንዲያገኙ የሚደረገው የአገሪቱ ዜጋና የስራ ብቃት ያላቸው ስለሆኑ ሳይሆን በዋናነት የፓርቲ አባልና ደጋፊ ለመሆን ባላቸው ፈቃደኝነት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት እውነተኛ አመለካከታቸውን ደብቀው የኢህአዴግ አባል ለመሆን የሚገደዱት ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ ሲሆን፣ እምነታቸውን አሳልፈው ላለመስጠት በመወሰን ከስራ እድል ተገልለው የሚቀሩት ወጣቶች ቁጥርም ከፍተኛ ነው፡፡

ከ 97 ዓ.ም ምርጫ በኋላ ኢህአዴግ ለወጣቱ ስራ ለመፍጠር በዋናነት የተነሳሳው ወጣቱ ተቃዋሚዎች ለሚቀሰቅሱት አመጽና ነውጥ ዋና ተቀጣጣይ ሃይል ነው ብሎ በማመኑ ቢሆንም እነዚህ ያለ እምነታቸው መስለው ለመኖር ሲሉ ስራ የተቀጠሩትም ሆኑ የፓርቲ አባል አንሆንም ብለው ከስራ ተገልለው የሚቀሩት ወጣቶች አመቺ ሁኔታ ሲያገኙ የአመጽና  የነውጥ ተባባሪ መሆናቸው አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ያለ ፍላጎታቸው ስራ ለማግኘት ሲሉ የፓርቲ አባል እንዲሆኑ የተገደዱትም ሆኑ በእምነታቸው ምክንያት ስራ አጥ እንዲሆኑ የሚደረጉት ወጣቶች ለስርዓቱ የሚኖራቸው ጥላቻና ንቀት ልዩነት አይኖረውም፡፡ ያለፍላጎቱ አባል እንዲሆን የተገደደው ወጣት ስራ አጥ እንደሆኑት ወጣቶች በይፋ ከተቃዋሚው ጎራ ጋር መሰለፍ ባይችል እንኳን በየመስሪያ ቤቱ ተሰግስጎ ህዝብን በመልካም አስተዳደር እጦት እያማረረ  መንግስትና ህዝብን ማጣላቱ አይቀርም፡፡

ባለፉት አስርት ዓመታት መንግስት በዋናነት ስራ የመፍጠር ሙከራ እያደረገ ያለው በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች አማካኝነት ቢሆንም እነዚህ ኢንዱስትሪዎች በአብዛኛው ከኮንስትራክሽን ሴክተሩ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ቋሚና በሂደት ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ተሸጋጋሪ ለመሆን አልቻሉም፡፡ እንደስማቸው ሁሉ አነስተኛና ጥቃቅን ሆነው ቀርተዋል፡፡ በዚህም ሆነ በሌሎቹ የኢኮኖሚ ዘርፎች እየተፈጠረ ያለው የስራ እድልም ከወጣቱ አጠቃላይ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ የአገራችን ኢኮኖሚ በስራ ቀጣሪነቱ ለሚታወቀው የማኑፋክቸሪንግ ሴክተር ተገቢ ትኩረት ሳይሰጥ በመኖሩም አገራችን የማምረቻ ፋብሪካዎች ሳይሆን የሱቅና የቢሮዎች አገር ሆናለች፡፡

በተለይም ኢህአዴግ ሲያራምደው በኖረው የእርሻ መር የኢኮኖሚ እስትራቴጂ ምክንያት አገሪቱ ዛሬም የኋላ ቀር እርሻ ጥገኛ ሆና ቀጥላለች፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ 85% ገበሬ የነበረው ህዝብ አሁንም ከ 25 ዓመት በኋላ 83%  ህዝብ ገበሬ ሆኖ በመቀጠሉ ከመሬት ጥበት ጋር በተያያዘ አብዛኛው የገጠር ወጣት ስራ አጥ ለመሆን ተገዷል፡፡ ይህም በመሆኑ ኢህአዴግ ሲፈራው የነበረው የከተማ ወጣት ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ እንደ አጋር ይቆጥረው የነበረው የገጠሩ ወጣትም የአመጽና የነውጥ ተቀጣጣይ ሃይል እየሆነ መምጣቱን በአሁኑ ወቅት በሃገራችን በተከሰተው የፖለቲካ ቀውስ በግልጽ እያየነው ነው፡፡

መንግስት በሃገራችን ትልቅ የሃብት ምንጭ በሆነው በመሬት ላይ ብቸኛ የባለቤትነት መብት ይዞ መቀጠሉም ተደራራቢ ችግሮችን እያስከተለ መጥቷል፡፡ በአንድ በኩል ህዝቡ ከመሬት ጋር ተጣብቆ እንዲኖርና ወደ ሌሎች የኢኮኖሚ ሴክተሮች እንዳይገባ በማድረግ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንቅፋት የሆነ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመሬት ጋር የተያያዘው ዘረፋና

የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ መንግስትን በሙስናና በኪራይ ሰብሳቢነት ረገድ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል፡፡ ከመሬት ጋር በተያያዘ እየተከሰተ ያለው የህገ- ወጥ ግንባታ፣ በልማት ምክንያት የሚፈጠር የዜጎች መፈናቀልና የካሳ ክፍያ ጉዳይ የህዝቡን ብሶትና ምሬት በማባባስ ረገድ ከፍተኛውን ሚና እየተጫወተ ነው፡፡ በተለይም በኦሮሚያ ክልል የመሬት ጉዳይ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ዋና ፖለቲካዊ ጉዳይ እየሆነ መምጣቱን እያዩን ነው፡፡ በአገራችን የመሬት ባለቤት ዜጎች ሳይሆኑ መንግስት የመሆኑ ጉዳይ "የመሬት ላራሹ" ጥያቄ ከመፈክር አልፎ በተግባር ያልፈታቸው ችግሮች ዛሬም እንዳሉ በገሃድ እያዩን ነው፡፡

በእኔ አመለካከት በኦሮሚያ ክልልም ሆነ በሌሎች የአገራችን አካባቢዎች የጥያቄ አቀራረቡ ወጥነትና ግልጽነት የሌለው ቢሆንም "መሬት ለዜጎች" የሚለው ጥያቄ የህዝቡ የዕለት ተዕለት ጥያቄ ሆኗል፡፡ በአሁኑ ወቅት በዋናነት በኦሮሚያ ክልልና በአገራችን ከተሞች ዙሪያ እንደምናየው መንግስት መሬትን እርባና በሌላው የካሳ ክፍያ ከህዝቡ እየቀማ እሱ ግን በአለም ላይ ታይቶ በማይታወቅ የገንዘብ መጠን እየቸበቸበው ነው፡፡ ቢያንስ ለመኖሪያ ቤትና ለእርሻ ስራ በዜጎች እጅ የሚገኘው መሬት ከነሙሉ ሙብቱ የዜጎች መሆን ሲገባው ሙሉ በሙሉ በመንግስት በመያዙ የፖለቲካ ቀውስ፣ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት መፈልፈያና የህዝብ ብሶት ዋና ምንጭ እየሆነ ነው፡፡ በእኔ አመለካከት ኢህአዴግና አንዳንድ ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅም ቆመናል የሚሉ የኦሮሞ ድርጅቶች "ነፍጠኞችን" ተጠቃሚ ሊያደርግ ይችላል በሚል የተሳሳተ ግምት መሬት የመንግስት እንዲሆን ሽንጣቸውን ገትረው ቢሟገቱም ከማንም በላይ የኦሮሞን ህዝብ ተጠቃሚ ሊያደርገው የሚችለው አጀንዳ ግን "የመሬት ለዜጎች" ጥያቄ ነው፡፡ መንግስት በሞኖፖል የያዘውን የመሬት ባለቤትነት ሙብት ቢያንስ በከፊል ለዜጎች ካላካፈለ በመንግስትና በህዝብ መካከል ያለው ግንኙነት መልኩን ቀይሮም ቢሆን የባላባትና የጭሰኛ ግንኙነት ሆኖ ይቀጥላል፡፡

## **2.6.2.** ኢኮኖሚን እንደ ብቸኛ የአገር ግንባታ መሳሪያ ማየት

ሌላው ከኢህአዴግ የልማታዊ መንግስትነት የተዛባ አስተሳሰብ ጋር የተያያዘው ችግር ኢኮኖሚያዊ ጥቅምንና እድገትን ብቸኛ የአገር ግንባታ (Nation building) መሳሪያ አድርጎ ማዬት ነው፡፡ ከአጠቃላዩ የኢህአዴግ የፕሮፖጋንዳ ቅኝት በግልጽ ለመረዳት እንደምንችለው ኢህአዴግ በግልጽ ባይናገረውም ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በማምጣት የህዝቡን ኑሮ ማሻሻል ከቻልኩ የህዝቡን የፖለቲካ የሙብት ጥያቄ ለረዥም ጊዜ ደፍቄ መቆየት እችላለሁ የሚል ቻይናዊ አቋም አለው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በግልጽ ባይናገረውም የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን የሚገኝበት የሶሽዮ- ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ዴሞክራሲንና የብዙሃን ፓርቲን ለሙተግበር ብቁ አያደርገውም ብሎ ያምናል፡፡ የኢህአዴግ እውነተኛ ዕምነት ለመጭዎቹ 20 እና 30 ዓመታት ያለምንም ትርጉም ያለው ተቀናቃኝ ሃይል በስልጣን ላይ መቆየትና በኢኮኖሚ ዕድገት አማካኝነት መካከለኛ ገቢ ያለው ህብረተሰብ በቅድሚያ ፈጥሮ በሂደት ዴሞክራሲንና የብዙሃን ፓርቲ ስርዓትን ለመፍጠር ነው የሚያስበው፡፡ ከዚህ አስተሳሰቡ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያን ህዳሴ እውን ለማድረግም ሆነ አንድ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችለኝ ዋናው ወኪል (Agent) በፖለቲካ ግርግር የማይደናቀፍና የማይታወክ የኢኮኖሚ እድገት ነው ብሎ አምኗል፡፡ ለህዝቡ በይፋ ባይናገረውም ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መሪ ካድሬዎቻቸውን ሲያስተምሩ የሚውሉት ይህንኑ ነበር፡፡

በእኔ አመለካከት ከልቡ እስካመነበት ድረስ ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ መያዙ ችግር አለው ብዬ አላምንም፡፡ በብዙ ታዳጊ አገሮች ይህ አይነቱ አስተሳሰብ እንደ አንድ አዋጭ የዕድገት አማራጭ ሃሳብ ተደርጎ ስለሚቀነቀን ኢህአዴግ የዚህ አቋም አራማጅ ቢሆን ችግር የለውም፡፡ ሙብቱም ነው፡፡ ችግሩ ያለው ኢህአዴግ ይህንን አቋሙን ለህዝብ በግልጽ አቅርቦ ለማሳመን መሞከር ሲገባው ከኢኮኖሚውና ከልማቱ ባላነሰ ዴሞክራሲም ለኢትዮጵያ አስፈላጊ የህልውና ጉዳይ ነው እያለ የማያምንበትንና በተግባር ሊያውለው የማይፈልገውን ሃሳብ ዕምነቱ አስመስሎ ለማሳመን መሞከሩ ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ አስመሳይነት በተቃዋሚው ጎራና በዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው ህዝብም በግልጽ የሚታወቅ ሃቅ ሆኗል፡፡ ኢህአዴግ የሚያስበውን የማይናገር፣ የሚናገረውን የማያደርግ ሴረኛና አስመሳይ ድርጅት ሆኖ በህዝቡ እንዲታይ ያደረገውም ይህ አይነቱ በቃልና በግብር የተለያዬ ድርጅት የመሆኑ ዕውነታ ነው፡፡ ኢህአዴግ ከእንግዲህ የቱንም ያህል ደግሞ

ደጋግሞ በመናገር ሊያሳምን የሚችለው ህዝብ የለም፡፡ ኢህአዴግ ከእንግዲህ ያለው አማራጭ በግልጽ ዴሞክራሲና መድብለ-ፓርቲ ለአገራችን አይበጁም ብሎ ህዝቡን ለማሳመን መሞከር፣ ወይም ዴሞክራሲም የልማትን ያህል አስፈላጊ ነው የሚለውን ዕምነቱን መሬት ላይ በተግባር ማሳዬት ነው፡፡

በኢህአዴግ የአስመሳይነት ባህሪ ምክንያት የህዝቡ ብሶትና ጥላቻ የበለጠ የሚባባስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ቁም ነገር ግን የኢትዮጵያ የአገር ግንባታ ሂደት የፖለቲካ መብት ተደፍቆ በኢኮኖሚ ለውጥ ብቻ የሚመጣ አለመሆኑ ነው፡፡ ህዝቡ የኢኮኖሚ ለውጥ መጥቶ ኑሮው እስከተሻሻለ ድረስ ለፖለቲካ መብት መከበር ብዙም ደንታ አይኖረውም ብሎ ማሰብ ስህተት ነው፡፡ እንዲያውም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለፖለቲካ መብት ጥያቄ የበለጠ ቀናኢ ሆኖ ለውጥ እንዲመጣ እየታገለ ያለው በኢኮኖሚ አቅሙ በአንጻራዊነት የተሻለ ደረጃ ላይ ያለው ህብረተሰብ ነው፡፡ በዚህ መንግስት ዘመን ሰርተው የከበሩ ባለሃብቶች ሳይቀሩ ለስርዓቱ ካላቸው ጥላቻ የተነሳ አመጽና ጦርነትም ቢሆን ተቀስቅሶ ይህ መንግስት እንዲወድቅ ሲመኙ የሚውሉ ናቸው፡፡ ድሃው ህዝብማ ቁርስና ራቱን በልቶ ማደርም ፋታ የማይሰጥ የዕለት ተዕለት አጀንዳ ስለሆነበት ስለመንግስት ለውጥ የማሰብ ዕድልም የለውም፡፡ ኢህአዴግ እንደሚያስበው በልማት ተጠቃሚ መሆን ብቻውን የአገር ግንባታ አጀንዳን የሚያሳካ ቢሆን ኖሮ በአሁኑ ወቅት በኢህአዴግ ዘመን በተሰራው አውራ-ጎዳና ላይ በሺዎች እየተመሙ፣ የተሰራውን ልማት እያቃጠሉና እያፈረሱ በመንግስት ላይ ያላቸውን ጥላቻ የሚገልጹ ወጣቶችን ባላየን ነበር፡፡ ሩቅ ሳንሄድ በራሳችን ጎረቤት አገሮች ከተከሰተው የአረብ ስፕሪንግ መማር ከቻልን እነ ሙባረክንና ጋዳፊን ጠራርጎ ከስልጣን ያስወገዳቸው ወጣት ኃይል በእነሱ ዘመን በተሰራ ስራ ለተሻለ የኑሮ ደረጃ የበቃ ትውልድ ነው፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ የአገር ግንባታ ሂደትም ሆነ የኢህአዴግ የአገር ህዳሴ ፕሮጀክት እውን ሊሆን የሚችለው የዜጐችን የፖለቲካዊ መብት በማክበርና የተሟላ የአገር ባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው በማድረግ እንጂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ልማትን በማምጣት ብቻ አይደለም፡፡ በአገሪቱ አስተማማኝ የፖለቲካ መረጋጋት ኑሮ በዜጐች ልቦና ውስጥ ትርጉም ያለው ሰላም ከሌለ የአገር ግንባታው ሂደትም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዳሴ የማሳካቱ ፕሮጀክት በቀላሉ ሊሳካ አይችልም፡፡ የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ቀውስ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ዕውነታ ነው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው አብዛኛዎቹ ችግሮች ኢህአዴግ እንደሚለው ከአፈፃፀም ጋር ብቻ የተያያዙ ችግሮች ሳይሆኑ ከተሳሳተ የፖሊሲ አቅጣጫ የሚመነጩ ችግሮችም ናቸው፡፡ ኢህአዴግ በዚህ ደረጃ የችግሩን መሠረታዊ ምንጭ መረዳትና አምኖ መቀበል ሲችል ብቻ ነው የመፍትሄው አካል መሆን የሚችለው፡፡

በአጭሩ ኢህአዴግ፡-

- የተሳሳቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎቹን በተገቢው ጊዜና ሁኔታ ከማረም ይልቅ በኮሚኒስታዊ የማስረፅ ስልት በሕዝቡ ላይ ለመጫን የሚጥር፣
- የሙያ፣ የዕውቀትና የስነምግባር ብቃት ሳይሆን የፓርቲ ታማኝነት ያላቸውን ደካማ ካድሬዎች በዙሪያው በመሰብሰብ ፖሊሲዎቹን የመፈፀም ብቃት ያጣና በመልካም አስተዳደር ዕጦት ህዝብን እያሰቃየ የሚገኝ፣
- ተቃዋሚ አስተሳሰብንና ተቃዋሚ ድርጅቶችን በማዳከምና በማጥፋት ፀረ-ዲሞክራሲ አቋም የሚያራምድ፣
- የአገሪቱን ችግሮች የማወቅም ሆነ መፍትሄ የማምጣት ብቃት ያለኝ እኔ ብቻ ነኝ የሚል የትምክህተኛነት ባህሪ የተጠናወተው አምባገነናዊ ድርጅት ነው፡፡

ስለሆነም የፖሊሲ ስህተቶችን፣ የአፈፃፀም ብቃት ማነስን፣ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን፣ ፀረ-ዴሞክራሲነትንና ትምክህተኝነትን ችግሮቹ አድርጐ የማይቀበል የኢህአዴግ ተሃድሶ የስልጣን እድሜ ከማራዘም ያለፈ ለወቅቱ የአገራችን

የፖለቲካ ችግር አስተማማኝና ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጣ አይችልም፡፡ ለወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ቀውስ ቀዳሚና ግማሹ መፍትሄም እስካሁን የተሰሩ ስህተቶችን በግልጽና በድፍረት አምኖ መቀበል መሆኑን ኢህአዴግ መረዳት አለበት፡፡

## 2.7. ተቃዋሚው ጐራ በወቅቱ የፖለቲካ ቀውስ ያለው ሚና

ከዚህ በላይ በዝርዝር የቀረቡ የኢህአዴግ ድክመቶችና አሉታዊ ድርጊቶች ህዝቡ በመንግስት ላይ ከፍተኛ ተቃውሞና ጥላቻ እንዲኖረው ያደረጉ ዋና ምክንያቶች ቢሆኑም ይህ የህዝብ ምሬት በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ሳይሆን በኃይልና በነውጥ ጭምር እንዲገለፅ በማድረግ ረገድ ግን ተቃዋሚው ጐራና ተቃዋሚውን ጐራ የሚደግፈው ህዝብ ድክመት ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ የወቅቱ የህዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴ እንደ ጥሩ የለውጥ ማግኛ ዕድል ብቻ ሳይሆን በአገር ህልውናና ደህንነት ላይ የባሰ አደጋ ሊያመጣ እንደሚችል ክስተት እንዲታይ ያደረገው በእኔ አመለካከት በተቃዋሚው ጐራና በደጋፊው ህዝብ ዙሪያ ያለው ድክመት ነው፡፡

ተቃዋሚው ጐራ ግልፅና የተብራራ አማራጭ ሃሣብ ቀርፆ፣ ህዝቡን በሃሣብ የበላይነት አሳምኖና በዙሪያው አደራጅቶ ከገዥው ፓርቲ የሚቃጣበትን አፈናና ተፅዕኖ በብቃት ተቋቁሞ ሰላማዊውና ሕጋዊውን ትግል በብቃት መምራት ባለመቻሉ የወቅቱ የህዝብ ትግል ከፍተኛ የሆነ የአስተሳሰብና የድርጅታዊ አመራር ክፍተት ተፈጥሮበታል፡፡ የወቅቱ ትግል ጠንካራ አማራጭ ሃሣብና ድርጅታዊ መዋቅር ባለው የፖለቲካ ፓርቲ ሳይሆን በአካባቢ የጐበዝ አለቃ፣ በውጭ አገር በሚገኙ ፅንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች ፕሮፓጋንዳ፣ በፌስ-ቡክ ጥሪና በአሉባልታ ዘመቻ ጭምር የሚመራ በመሆኑ አገሪቱን ወዴት አቅጣጫ እንደሚወስዳት የማይታወቅ ትግል ሆኗል፡፡

በትግሉ ዙሪያ ተሣትፎ እያደረገ ያለው ህዝብ ኢህአዴግ እንደሚለው የተሃድሶ ለውጥ ብቻ ሳይሆን የመንግስት ለውጥ የሚፈልግ መሆኑ በግልፅ እየታየ ቢሆንም የሚፈለገው ለውጥ ኢህአዴግን ከስልጣን ከማውረድ ባሻገር ከኢህአዴግ የተሻለ መንግሥትና ስርዓት እንዴትና በምን ሁኔታ ሊያመጣ እንደሚችል ግን በግልፅ የተቀመጠ አቅጣጫ የለውም፡፡ ይህም በመሆኑ የትግሉ እንቅስቃሴ የተሻለ ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ዕድልና አጋጣሚ ሳይሆን የባሰ አገራዊ ቀውስ ሊፈጥር እንደሚችል አደጋ በስጋት እየታዬ ነው፡፡ የአገሪቱ ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ በእንዲህ ዓይነት ግራ-ቀኙን ገደል ባደረገ አጣብቂኝ ውስጥ እንዲገባ ያደረገው አንዱ ምክንያት የጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ አለመኖር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በተቃውሞ ትግሉ ዙሪያ ያሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ህዝቡን በስሜትና በምሬት እየመሩ ከሚገኙት የአካባቢ የጐበዝ አለቃዎች የተሻለ ሚና ያላቸው ባለመሆኑ በወቅቱ የህዝብ ትግል እንቅስቃሴ የወረቀት መግለጫ ከማውጣት ያለፈ ቦታና ሚና የሌላቸው /Irrelevant/ ኃይሎች ሆነዋል፡፡

ስለወቅቱ የአገራችን ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ በድፍረትና በሃቅ መነጋገር ካለብን የመንግስት ስልጣንን ተረክቦ አገርን በብቃት ማስተዳደር ይቅርና ከገዥው ፓርቲ የሚቃጣበትን ጥቃት በአግባቡ ተቋቁሞ የራሱን ሕልውና አስጠብቆ መቀጠል የሚችልም ሆነ የሕዝቡን ትግል በአግባቡ አቅጣጫ አስይዞ ሊመራ የሚችል አንድም ጠንካራ ድርጅት በአገራችን የለም፡፡ ኢህአዴግ ለአለፉት 25 ዓመታት በብቸኝነት አንቀጥቅጦ የገዛንም ሆነ በአሁኑ ወቅት ህዝቡ ያለ ድርጅታዊ አመራር በተበታተነና ባልተቀናጀ ሁኔታ በመንግሥት ላይ ለማመፅ የተገደደው ያለምክንያት ሳይሆን በድርጅታዊ ጥንካሬውና በአስተሳሰብ ጥራቱ እስከአሁን ሕዝብ በሙሉ ልቡ አምኖ የተቀበለው ፓርቲ ባለመኖሩ ነው፡፡ የቱንም ያህል የኢህአዴግን ስህተትና ኃጢያት ስንቆጥር ብንውል፣ የቱንም ያህል ኢህአዴግ ስልጣኑን እንዲያጣና አዲስ የመንግስት ለውጥ እንዲመጣ ስንመኝና ስንጠይቅ ብንውል ያለጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ መኖር ሊመጣ የሚችል አስተማማኝና ዘላቂ ለውጥ አይኖርም፡፡

በእኔ አመለካከት የተቃዋሚው ጐራ መሠረታዊ ድክመት የሚመነጨው ከሦስት አቅጣጫ ነው፡፡ አንደኛ - የሕዝቡንና የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ ያገናዘበ ጥራት ያለው አማራጭ ሃሣብ ካለመኖር፣ ሁለተኛ - ከተሳሳተ የትግል ስልትና

አቀራረብ፣ ሦስተኛ - ጠንካራ ድርጅት ለመፍጠር የሚያስችል ሁለንተናዊ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ካለመሆን የሚመነጭ ነው።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እስከአሁን እንደሚያደርጉት እራሳቸውን ጠንካራና ሃቀኛ አስመስለው ለሕዝብ በማቅረብ ያለ አግባብ ከመመፃደቅ ይልቅ ውስጣቸውን በሃቅ ገምግመውና ድክመታቸውን አርመው በአዲስ መልክ ተጠናክረው መውጣት አለባቸው። ከስሜታዊነት፣ ከጭፍን ጥላቻ፣ ከእወደድ-ባይነት፣ ከዘረኝነትና ከአሉባልታ የፀዳ ዝርዝርና የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በአግባቡ የተገነዘበ አማራጭ ሃሣብ በማቅረብ፣ ሰላማዊ ትግሉ በጉልበት፣ በጊዜ፣ በእውቀት፣ በገንዘብ፣ በአካልና በሕይወት ጭምር የሚጠይቀውን መስዋዕትነት በፅናት በመክፈል ተቃዋሚው ጐራ በአዲስ ተነሳሽነት ተጠናክሮ መውጣት አለበት።

በቅድሚያ ራስን ሳያበቁና ሳያዘጋጁ መንግሥት ስልጣኑን እንዲያጣ መፈለግ ከፈረሱ ጋሪው ዓይነት ቅደም ተከተሉን የሳተ ስልት መሆኑን በመገንዘብ የተቃዋሚው ጐራ የወቅቱ አጣዳፊና አሳሳቢ አጀንዳ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ በአገር ውስጥ መፍጠር መሆን አለበት። ተመሳሳይ አደረጃጀትና የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸው ፓርቲዎች ህብረት ወይም ውህደት በመፍጠር፣ ይህንን ማድረግ የማይችሉ ፓርቲዎች ራሣቸውን በተናጠል በማጠናከር፣ ይህንንም ማድረግ ካልተቻለ በበቂ ቅድመ ዝግጅት አዲስ ፓርቲ ጭምር በማቋቋም ተቃዋሚው ጐራ በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ትርጉም ያለው ሚና እንዲጫወት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተቃዋሚው ጐራ በአስቸኳይ ተጠናክሮ በአሁኑ ወቅት የሚታየውን የተበታተነና ያልተቀናጀ የሕዝብ ትግል በአግባቡ አቅጣጫ አስይዞ መምራት የማይቻል ከሆነ በኢህአዴግ "ጥልቅ" ተሃድሶም ሆነ በሕዝቡ የተጠናጠል ትግል የሚመጣ አስተማማኝና ዘላቂ ለውጥ ሊኖር አይችልም። እንዲያውም የወቅቱን የተበታተነ የሕዝብ ትግል በብቃትና በኃላፊነት ስሜት በአግባቡ መምራት የሚችል ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ሳይፈጠር ወይም ኢህአዴግ የሕዝቡን መሠረታዊ ጥያቄዎች ከልቡ ተቀብሎ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ሳይወስን የወቅቱ የፖለቲካ ቀውስ የበለጠ እየተባባሰ ከመጣ ማናችንም ልንገምተው በማንችለው ፍጥነት አገራችን ሕልውናዋን ወደሚፈታተን ቀውስ ልትገባ ትችላለች።

እንዲህ ዓይነቱ አደጋ በእኛ አገር አይከሰትም ብሎ መገመት በሕዝባችን ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየተባባሰ የመጣውን የጥላቻና የፅንፈኝነት ስሜት በአግባቡ ካለመረዳት የሚመነጭ ይመስለኛል። እንኳንስ ለ 25 ዓመታት ልዩነት ሲሰበክባት በኖረችዋና በውስጧ በርካታ የአስተሳሰብ፣ የብሄርና የኃይማኖት ቅራኔን አርግዛ በምትገኘው በኛ አገር፣ አንድ ቋንቋና አንድ ሃይማኖት ባላቸው አገሮች በአረብ ስፕሪንግ አማካኝነት የተቀሰቀሱ ብጥብጦች አገራትን ምን ያህል ወደ መንግስት የለሽነትና ወደ ዘግናኝ የርስ-በርስ ጦርነት እንዳስገቡ ማዬት ችለናል።

ስለሆነም ተቃዋሚው ጐራ በኃይልና በነውጥ እንቅስቃሴም ሆነ በሌላ አቋራጭ መንገድ ስልጣን ለማግኘት ከመሞከር ይልቅ-በአገሪቱ ትርጉም ያለው ብሄራዊ መግባባትና እርቅ እንዲፈጠርና የፖለቲካ ምህዳሩ ትርጉም ባለው መጠን እንዲሰፋ በመንግስት ላይ ጠንካራ ተፅዕኖ መፍጠር አለበት። ኢህአዴግ በጠንካራ የሕዝብ ትግል እንጂ በጥያቄ ሊለወጥ የማይችል ፀረ-ዴሞክራሲ አምባገነናዊ መንግስት መሆኑን በመገንዘብም ተቃዋሚው ጐራ ሕዝቡን በዙሪያው በማደራጀትና ጠንካራ ሕጋዊና ሰላማዊ ትግል በማካሄድ ስርዓቱ ወደደም ጠላም የሕዝቡን ጥያቄ ለመቀበል የሚገደድበትን ትግል አጠናክሮ መቀጠል ይጠበቅበታል።

ተቃዋሚው ጐራ ከእስካሁኑ ድክመቱ በአግባቡ ተምሮ እራሱን በአጭር ጊዜ አጠናክሮ መውጣት ከቻለ በአሁኑ ወቅት በስርዓቱ ዙሪያ የሚታዬው ሁለንተናዊ ድክመትም ሆነ በሕዝቡ ውስጥ እየታዬ ያለው ከፍተኛ የለውጥ ፍላጐት ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ጥሩ አጋጣሚ ይሆንለታል። ይህንን ዕድል በአግባቡ ከተጠቀመበት ተቃዋሚው ጐራ በመጭው የ 2012 አገራዊ ምርጫ ሲቻል የመንግስት ለውጥ፣ ካልተቻለም ከፍተኛ የፓርላማና የክልል ምክር ቤቶች መቀመጫ በማሸነፍ ራሱን ትርጉም ወደ አለው የፖለቲካ ኃይል ማሸጋገር ይችላል። በ 2012 ይህንን ዓይነቱን ውጤት

ለማሳካትም ከፊታችን በ 2010 በአዲስ አበባ ከተማ በሚካሄደው የክልል ምክር ቤት ምርጫ በበቂ ዝግጅት በመሳተፍ ምርጫውን በሕዝቡ ውስጥ አዲስ የሰላማዊ ትግል ተነሳሽነት ለመፍጠርና ለ 2012 አገራዊ ምርጫ የላቀ ውጤት የመስፈንጠሪያ ሂደት አድርጐ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ይህንን የአዲስ አበባ ምርጫም ኢህአዴግ ከዚህ ሁሉ የሕዝብ የተቃውሞ እንቅስቃሴና “ጥልቅ” ብሎ ከጠራው የተሃድሶ እንቅስቃሴ በኋላ ምን ያህል በተጨባጭ መለወጥ እንደቻለ አንድ የመፈተሻ መድረክ አድርጐ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ይህንን ዓይነት ቀጣይነትና ትርጉም ያለው የሕዝብ ተሳትፎ የሚታይበት ጠንካራ ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ ዝግጅቱ ነገ ሳይሆን ዛሬ መጀመር አለበት፡፡ ተቃዋሚው ጐራ ይህንን ኃላፊነቱን በአግባቡ መወጣት የሚችል ከሆነ የሕዝባችን የለውጥ ፍላጐት ኢህአዴግን ከስልጣን በማውረድ ብቻ ሳይሆን ከኢህአዴግ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በማምጣት ሊሳካ ይችላል፡፡

የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው ህዝብም ብዙ በደል የተሸከመና ለውጥ ፈላጊ ህዝብ ሆኖ እያለ ተደራጅቶ የመታገልን የማይተካ ጠቀሜታ በአግባቡ ባለመገንዘቡ እስከአሁን ጠንካራ ፓርቲ መፍጠር አልቻለም፡፡ ህዝቡ ስርዓቱን ከማማረርና ለውጥ ፈላጊ ከመሆን ባሻገር ለራሱና ለአገሩ ጠቃሚ አማራጭ ሃሣብ ባላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ በመደራጀት ሃሣቡን፣ ጉልበቱን፣ ገንዘቡን፣ ዕውቀቱንና ጊዜውን በአግባቡ ቢያዋጣ ኖሮ ዛሬ ላይ የተበታተነ የትግል እንቅስቁሴውን በአግባቡ አቀናጅቶ የሚመራ/የሚመሩ ፓርቲዎች በኖሩት ነበር፡፡ ሕዝቡ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ሊፈጠር የሚችለው ከየትም ሳይሆን ከራሱ ተጨባጭ ተሳትፎና የትግል ውጤት መሆኑን ባለመገንዘብ ከሩቅ ሆኖ ድክመታቸውን በመዘርዘር ሲተቻቸውና ሲያማቸው ስለሚውል ተጠናክረው ሊወጡ አልቻሉም፡፡

ከሁሉም በላይ በራሱ በህዝቡ ውስጥ ሆነው በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ ለውጥ ለማምጣት የሚታገሉትን ፓርቲዎች አቅፎና ደግፎ ከማጠናከር ይልቅ ሩቅ ናፋቂ በመሆን በአውሮፓና በአሜሪካ ያሉ ተቃዋሚዎች መጥተው ነፃ እንዲያወጡት ሲናፍቅ ስለሚውል የኢህአዴግን አፈና ተቋቁሞና ትግሉን በአግባቡ መርቶ ለድል የሚያበቃ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ በአገር ውስጥ መፍጠር አልቻለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከእውነተኛ የሕዝብ ብሶትና የለውጥ ፍላጐት የመነጨውን የወቅቱን የሕዝብ ትግል አሉባልታና የጥላቻ አመለካከት በማሰራጨት ሊመሩት ሲሞክሩ የሚታዩት አገር ውስጥ የሚገኙት ሳይሆኑ ከአትላንቲክ ማዶ የሚገኙት ፅንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች ሆነዋል፡፡ በእኔ አመለካከት ህዝቡ የቱንም ያህል በስርዓቱ ላይ ጥላቻ ቢኖረው፣ ከጥላቻም አልፎ የቱንም ያህል ለትግል ተነሳስቶ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ለመክፈል ቢወስን የሚያካሂደው ትግል የጠራ አመለካከትና ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር ባለው በአገር ውስጥ በሚገኝ የፖለቲካ ፓርቲ እስካልተመራ ድርስ የትም ሊደርስ አይችልም፡፡

በአሁኑ ወቅት ህዝቡን በተለያዩ ተፅዕኖዎችና የአፈና ድርጊቶች እያሰቃየው የሚገኘው ገዥው ፓርቲም ሆነ ይህንን ዓይነቱን ስርዓት በአግባቡ ታግለው መለወጥ ያቃታቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከየትም የመጡ ሳይሆኑ ከዚሁ ህዝብ የተፈጠሩና የህዝቡ የፖለቲካ የአስተሳሰብ ደረጃና ባህል መገለጫዎች ናቸው፡፡ በአንድ አገር ጥሩ ስርዓት ሲኖር የሚጠቀመው፣ መጥፎ ስርዓትም ሲኖር የሚጐዳውና ዋጋ የሚከፍለው ህዝብ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በአንድ አገር የሚገኙ ፓርቲዎችን የመመስረት፣ ከመሰረተም በኋላ የማጠናከርና ለመንግሥት ስልጣን የማብቃት፣ አልጠቀሙኝም ብሎ ሲያምንም ከስልጣን የማውረድና በሌላ የመተካት ኃላፊነት ያለበት ሕዝቡ ነው፡፡ አንድ ሕዝብ ጠንካራና አገልጋይ የሆነ ስርዓት ሲኖረው የሚኮራውንና የሚመካውን ያህል ደካማና ጨቋኝ ስርዓት ሲኖረውም በዚያው መጠን ሊያፍርና ሊቆጭ ይገባዋል፡፡

አንድን ሕዝብ እንደ ሕዝብ መተቸት በተለምዶ የፖለቲካ ስህተት ተደርጎ ቢታይም አንድ ሁልጊዜ ጨቋኝ ስርዓቶች በጫንቃው ላይ እየተፈራረቁ የሚገዙትና እነዚህን ጨቋኝ ስርዓቶች የሕዝብ አገልጋይ በሆነ ስርዓት መተካት የተሳነው ሕዝብ ያለጥርጥር የለውጥ ኃይል መሆን የተሳነው ደካማ ሕዝብ ነው፡፡ የለውጥ ኃይል ለመሆን የበቃ ሕዝብ ግን ጌታውን ሳይሆን አገልጋዩ የሚሆነው ስርዓት ይፈጥራል፡፡ በእኛ አገር ያለውን ተጨበጭ ሁኔታ ስናይ ግን ሕዝብ እስከአሁን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት

የለውጥ ኃይል አልሆነም፡፡ ባለፉት 40 ዓመታት ሦስት ገዥዎችን መቀያየር ቢችልም እስከአሁን ገዥዎችን በገዥዎች እንጂ ገዥዎችን በአገልጋይ ስርዓቶች መቀየር አልቻለም፡፡

በአሁኑ ወቅትም ተቃዋሚውን ጐራ በሚደግፈው ሕዝብ ውስጥ ያለው ትኩረትና አዝማሚያ መንግሥትን በሌላ መንግሥት የመቀየር እንጂ ገዥን በአገልጋይ የመቀየር አይመስልም፡፡ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከስልጣን እንዲወገድ በሕይወቱ ጭምር ዋጋ እየከፈለ ያለው ሕዝብ ወደፊት ኢህአዴግን ተክቶ ስልጣን የሚይዘው ፓርቲ ማንና ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይቅርና ማሰብም የሚፈልግ አይመስልም፡፡ ነገር ግን ተተኪ የፖለቲካ ኃይል በአግባቡ ባለተዘጋጀበትና የሕዝቡ ትግል የሚሠራውን በሚያውቅ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት በማይመራበት ሁኔታ በስሜትና በአመፅ ብቻ አንድን ስርዓት ማፍረስ መንግስት የለሽነትንና መቋጫ የሌለው የርስ በርስ ጦርነትን በመቀስቀስ ገዥ ፓርቲን ብቻ ሳይሆን አገርን የሚያፈርስ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ አደጋ ከፊታችን ያለ ቢሆንም ህዝቡ ግን በአፈና ካማረረው ስርዓት ለመገላገል ስለቸኮለ ብቻ ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን የባሰና አስከፊ ጣጣ ሊረዳው ቀርቶ ሊያስበው አልቻለም፡፡

በሕዝቡ ውስጥ ያሉ የጥላቻ ስሜቶች ከአግባብ በላይ በመለጠጣቸው ምክንያት በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ የኦሮሚያ አካባቢዎች "ቅኝ ተገዥዎችና ሁለተኛ ዜጋ ሆነናል" በሚል እየተፈጠረ ያለው የከረረ ስሜትና በአንዳንድ የአማራ አካባቢዎች "የዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈፀመብን ነው" በሚል እየተሰራጨ ያለው አደገኛ ፕሮፖጋንዳ ወዴት አቅጣጫ ሊወስደን እንደሚችል ለመረዳት ከሞከርን አገራችን ሶማሊያ ወይም ሩዋንዳ ልትሆን አትችልም ብሎ መደምደም የሚቻል አይመስለኝም፡፡ አገራችን ወደዚህ ዓይነቱ በቀላሉ መውጣት የማይቻልበት አደጋ ውስጥ እንዳትገባና በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንድትሸጋገር ከተፈለገ ህዝቡ ቢያንስ የሚከተሉትን አራት ኃላፊነቶች በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡

<u>አንደኛ</u>- አንድ ሕዝብ የቱንም ያህል ግፍና ጭቆና ቢደርስበትና ከዚያ ግፍና ጭቆና ለመላቀቅ ቢፈልግ - ትግሉን በድርጅት ዙሪያ ያላስተባበረ ሕዝብ ፍላጐቱን ሊያሳካ እንደማይችል በመገንዘብ በአስቸኳይ በፓርቲዎች ዙሪያ መደራጀት አለበት፡፡ ሕዝቡ አሁን በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙት ደካማ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሆነ ተአምር ለውጥ ያመጡልኛል ብሎ ዳር ቆሞ ከመጠበቅ ይልቅ በውስጣቸው እየገባ ሊፈትሻቸውና ሊያጠናክራቸው ይገባል፡፡ ሕዝቡ ራሱን በፓርቲ መስራችነት፣ በፓርቲ አባልነት፣ በፓርቲ አመራርነትና በምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪነት ተሳታፊ በማድረግና የተደራጀባቸውን ፓርቲዎች በጉልበቱ፣ በጊዜው፣ በእውቀቱና በገንዘቡ በመርዳት ትርጉም ባለው መጠን ሊያጠናክራቸው ይገባል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሕዝቡ ትግል ዙሪያ የተፈጠረውን የድርጅት የአመራር ክፍተት በመረዳትና ድርጅት በአንድ ሕዝብ የፖለቲካ ትግል ውስጥ ያለው ሚና የማይተካ መሆኑን በመገንዘብ የጠንካራ ድርጅት መኖርን ጉዳይ ወቅታዊና ቀዳሚ አጀንዳው ሊያደርገው ይገባል፡፡

<u>ሁለተኛ</u>- እስከአሁን በነበረው የፖለቲካ ትግል ሂደት አብዛኛውን ጊዜ ሕዝብ ፓርቲዎችን ሲደግፍ የሚታየው የግለሰቦችን ዕውቅናና ዝና፣ ስሜታዊ ቅስቀሳንና ጊዜያዊ ጀብደኛነትን መመዘኛ አድርጐ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ እስከአሁን ከሁለትና ከሦስት ዓመት በላይ የሕዝቡን ትኩረት ስበው ተጠናክረው መውጣት የሚችሉ ፓርቲዎች ማግኘት አልቻለም፡፡ ይህ ሁኔታ ተለውጦ ሕዝቡ የጠንካራ ፓርቲ ባለቤት መሆን ከፈለገ ብቸኛ መመዘኛው ፓርቲዎቹ ለአገርና ለሕዝብ ያላቸው አማራጭ ሃሣብና ሃሣባቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ያላቸው ጥንካሬና ቁርጠኛነት መሆን ይገባዋል፡፡

<u>ሦስተኛ</u>- ኢህአዴግ ያለ ጠንካራ የሕዝብ ትግል ስልጣኑን ለመልቀቅ ወይም ለማጋራት ፍቃደኛ የማይሆን ድርጅት መሆኑን በመገንዘብ ህዝቡ የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ነገር ግን በአንድ በኩል ሊካሄድ የሚገባው ትግል ፍፁም ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ የትግል ስልት መመራት ያለበት፣ በሌላ በኩል በአገራችን የፖለቲካ ትግል ተጨባጭና ዘላቂ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉት በውጭ አገር እየኖሩ የነውጥና የትጥቅ ትግል ስልትን የሚሰብኩ አክራሪ የፖለቲካ ኃይሎች ሳይሆኑ አገር ውስጥ ሆነው በሰላማዊና በህጋዊ መንገድ የሚታገሉ ፓርቲዎች መሆናቸውን ከልቡ አምኖ ሊቀበል ይገባል፡፡ ከአሁን በኋላ

በአገራችን የፖለቲካ ስልጣን በሕዝብ ምርጫ ካርድ ብቻ እንጂ በጠመንጃ አፈሙዝና በሌላ አቋራጭ መንገድ መያዝ እንደሌለበት ከማንም በላይ አምርሮ መቃወምና መታገል ያለበት ሕዝቡ ነው፡፡

<u>አራተኛ</u>- በአገራችን መምጣት ያለበት ለውጥ ሁሉንም የአገሪቱን ሕዝቦች ያሳተፈና በውጤቱም ሁሉንም የአገሪቱን ሕዝቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሕዝቡ አጀንዳና ፍላጐት በተከፋፈለበት ሁኔታ በስርዓቱ ላይ ተገቢውን ጫና ማሳደር ስለማይቻል ሕዝቡ የሚያነሳቸው አጀንዳዎች ከአባቢያዊ ጉዳዮች ይልቅ አገር አቀፋዊ ይዘት ያላቸው፤ አንድን ሕዝብ ወዳጅ ሌላውን ሕዝብ ጠላት አድርገው የማያዩ፤ የፖለቲካ ፓርቲንና ሕዝብን ለያይተው የሚያዩ፤ ከአሉባልታ፣ ከዘረኝነትና ከጥላቻ ቅስቀሳና ድርጊት ፈፅሞ የፀዱ፣ የመንግስትንም ሆነ የግለሰቦችን ንብረት ከማውደም የተቆጠቡ መሆን ይገባቸዋል፡፡

የምንታገለውን ስርዓት የምናይበት መንገድ ጭምር ምክኒያታዊና ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባዋል፡፡ የምንታገለው ኢህአዴግን ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ለማጥፋት ሳይሆን በነፃና ፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ እየተዳኘ የአገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ሂደት አካል ሆኖ እንዲቀጥል መሆኑን፤ ትግላችንም ለሰላምና ለእኩልነት እንጂ ኢህአዴግንና አባላቱን ለመበቀልና ለመቅጣት አለመሆኑን ከወዲሁ ማረጋገጥ አለብን፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ከስሜታዊነት የፀዳ ስልት የትግሉን ሂደትም ሆነ የውጤቱን ይዘት ዘላቂና አስተማማኝ ያደርገዋል፡፡ አሸናፊና ተሸናፊ ሳይሆን ለአዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁላችንንም የጋራ አሸናፊዎች ያደርገናል፡፡ በአጠቃላይ መንግስት፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሕዝብ እነዚህን የየበኩላቸውን ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት ከቻሉ አገራችንን ከእርስ በርስ ጦርነትና ከመንግሥት የለሽነት አደጋ መታደግ ብቻ ሳይሆን የእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ባለቤት እንድንሆን ማድረግ ይቻላል፡፡

## 3. ማጠቃለያ

የወቅቱን የአገራችንን ሁኔታ በተመለከተ ገዥው ፓርቲ በአሁኑ ወቅት የያዘው አቋም የችግሩን ትክክለኛ ምንጭ ያልተረዳና የችግሩን ትክክለኛ የመፍትሄ አቅጣጫም ያልያዘ ነው፡፡ የወቅቱ ችግር በዋናነት ከተሳሳቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎች፣ ከከፍተኛ የአፈፃፀም ብቃት ማነስ፣ ከፀረ-ዴሞክራሲና የትምክህት አመለካከት የመነጨ መዋቅራዊ /Systemic/ ችግር ቢሆንም ኢህአዴግ ግን የችግሩን ምንጭ ከመጠን በላይ አሳንሶና አኮማትሮ በዋናነት ከሙስናና ከቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረድ ጋር የተያያዘ የመልካም አስተዳደር ችግር አድርጐ አቅርቦታል፡፡

የችግሩን መፍትሄ በተመለከተም ኢህአዴግ በራሴ ላይ "ጥልቅ" የተሃድሶ ዘመቻ በማካሄድና እንደገና ተጠናክሬ በመውጣት ችግሩን እራሴው እንደፈጠርኩት እራሴው እፈታዋለሁ እያለ ነው፡፡ ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት በአገራችን የተፈጠረውን ችግር በርግጠኛነት ለመፍታት ከፈለገ በእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች ላይ ያለውን አቋም በአግባቡ መርምሮ ማስተካከል አለበት፡፡

የችግሩ ምንጭ ሙስናና የአፈፃፀም ብቃት ማነስ ብቻ ሳይሆን በዋናነት የፖሊሲ ስህተትና የፀረ-ዴሞክራሲ አመለካከት ጭምር መሆኑን፤ ችግሩን ለመፍታት የሚቻለውም በኢህአዴግ ውስጥ ጥልቅ ተሃድሶ በማድረግ ብቻ ሳይሆን ከሕዝቡና የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ከሚወክሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ሲቪል ማሕበራት ጋር በጋራ በመምከርና በመተባበር መሆኑን ከልቡ አምኖ መቀበል አለበት፡፡ ኢህአዴግ ከእንግዲህ እስከአሁን በመጣበት መንገድ አገሪቱን በተረጋጋ ሁኔታ እየገዛ ሊቀጥል የሚችልበት ዕድል እየተሟጠጠ መምጣቱን በመገንዘብ ከሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ጋር እየተመካከረ፣ እየተደራደረና እየተባበረ ለመሥራት መወሰን አለበት፡፡ የአገሪቱ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት በእኔ መንገድ ብቻ ነው ከሚለው የፀረ-ዴሞክራሲና የትምክህተኛነት አመለካከት ተላቆ ሌሎችንም የአገሪቱ ችግሮች የመፍትሄ አካሎች አድርጐ መቀበል አለበት፡፡ መቀበልም ብቻ ሳይሆን እነዚህ ሁኔታዎች እንዲለወጡ የሚያስችል ተጨባጭ እርምጃ በፍጥነትና በግልፅነት መውሰድ አለበት፡፡

በእኔ አመለካከት ኢህአዴግ የወቅቱን የአገሪቱን የፖለቲካ ችግሮች ከልቡ ለመፍታት ከፈለገ ይህንን ፍላጐቱን የሕዝብ እምነትና ሕጋዊነት ባለው መንገድ ለማስፈፀም የሚከተሉትን ሶስት እርምጃዎች በአስቸኳይ መውሰድ አለበት፡፡

<u>አንደኛ</u> - ኢህአዴግ ከልቡ ሊለወጥ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ጥያቄ በጥያቄነት መቀጠሉ የማይቀር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ወቅት ከልቡ ለመለወጥ ቢወስን እንኳ የሕዝቡን ተቀባይነት በቀላሉ ሊያገኝ አይችልም፡፡ ኢህአዴግ የችግሩን ክብደት በአግባቡ የተረዳው ባይመስልም ለአለፉት 25 ዓመታት ያራመደው የተሳሳተ የፕሮፓጋንዳ ስልት በሕዝብና በመንግሥት መካከል ያለውን ዕምነት በቀላሉ እንዳይጠገን አድርጐ በጣጥሶታል፡፡ መንግሥት ከእንግዲህ ውሸት እና የተጋነነ ፕሮፖጋንዳ በማሰራጨት ብቻ ሳይሆን እውነትም ተናግሮ የማይታመንበት ደረጃ ደርሷል፡፡ ይህ ሁኔታ ተለውጦ ኢህአዴግ ስለሚሠራውና ስለሚናገረው ነገር በሕዝቡ መታመንና መደመጥ ከፈለገ በቅድሚያ ለአለፉት 25 ዓመታት የተጠቀመበትን የፕሮፖጋንዳ ስልት መቀየርና በፌዴራልና በክልል ደረጃ የተቆጣጠራቸውን መገናኛ ብዙሃን አሠራር መሠረታዊ በሆነ ደረጃ መለወጥ አለበት፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑን አሠራር ብቻም ሳይሆን በእነዚህ መገናኛ ብዙሃን ለዓመታት ተሰግስገው በተሳሳተና አሰልቺ በሆነ የፕሮፓጋንዳ ስልት መንግሥትንና ሕዝብን የማራራቅ ሚና ሲጫዎቱ የኖሩትንና የህዝብ አይነ-ጥላ /Allergy/ እየሆኑ የመጡ ካድሬ-ጋዜጠኞችን ጠራርጐ ማስወገድ ይኖርበታል፡፡ ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነት ተጨባጭ እርምጃ በመውሰድና ያልተዛባና ያልተጋነነ መረጃ በማቅረብ በቅድሚያ የሕዝቡን እምነት ማግኘት ካልቻለ የወቅቱን የፖለቲካ ቀውስ በዘላቂነት ማረጋጋትም ሆነ ሕዝቡ ቀጥተኛ ተሣታፊ የሚሆንበት የለውጥ ሂደት ውስጥ አገሪቱን ማስገባት አይችልም፡፡

<u>ሁለተኛ</u>- ኢህአዴግ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በአስቸኳይ የውይይት፣ የምክክርና የድርድር ሂደት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ በዚህ ሂደትም አሁን ለምንገኝበት የፖለቲካ ቀውስ ያበቁን ችግሮች የትኞቹ እንደሆኑ ለይቶ ማስቀመጥና ወደፊት የፖለቲካ ምህዳሩን በሚፈለገው መጠን ለማስፋትና ህዝቡን በምርጫ አማካኝነት እውነተኛ የስልጣን ባለቤት ለማድረግ መሻሻል የሚገባቸው ህጎችና ተቋማት የትኞቹ እንደሚሆኑ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር የጋራ መተማመን ላይ መድረስ ያስፈልጋል፡፡

<u>ሶስተኛ</u>- በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች ድርድር የሚገኘውን ውጤት ሕጋዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ ለመፍታትና በመንግስትና በህዝብ፣ በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል ያለውን ያለመተማመን ክፍተት ለማጥበብ ከተፈለገ መንግሥት ሁለት ፖለቲካዊ ኃላፊነቶችን ሊያስፈጽም የሚችል አንድ ገለልተኛ ኮሚሽን በአዋጅ ማቋቋም አለበት፡፡ የሚቋቋመው ኮሚሽን ከገዥውም ፓርቲ ሆነ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ገለልተኛ ሆኖ የሚደራጅና የሚከተሉትን ሁለት ዓላማዎች ለማስፈፀም የሚቋቋም ኮሚሽን መሆን አለበት፡፡

አንደኛው ዓላማ- እስከአሁን በአገራችን በተከሰተው የግጭትና የአለመግባባት የፖለቲካ ሂደት ቅራኔ ውስጥ የገቡ የሕብረተሰብ ክፍሎችንና የፖለቲካ ኃይሎችን በማቀራረብና በማግባባት በአገራችን ጠንካራ የሆነ ብሄራዊ መግባባትና እርቅ እንዲፈጠር ማድረግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ዓላማ- በገዢው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል የሚደረስበትን የድርድር ውጤት መሰረት አድርጎ በ 2010 በአዲስ አበባ ከተማና በ 2012 በአገራችን የሚካሄደውን ብሄራዊ ምርጫ በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይሆናል፡፡ የሚቋቋመው ኮሚሽን ዝርዝር ቅርፅና ይዘትም በገዥው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች የጋራ ምክክር የሚዎሰን መሆን አለበት፡፡

የዚህ ኮሚሽን ዓላማዎች በአግባቡ ተፈጻሚነት አግኝተው ህዝቡ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ የስልጣን ባለቤትነቱ እንዲረጋገጥ ከተፈለገም ኢህአዴግ ለመጭዎቹ 20 እና 30 ዓመታት አገሪቱን እየገዛ ለመቀጠል ያለው ፍላጎት ከወቅቱ የአገራችን ህዝብ ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የማያዋጣ የከሸፈ ምኞት መሆኑን ተገንዝቦ በተቃዋሚ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ ላይ ምንም ዓይነት እንቅፋት ባለመፍጠር ብቻ ሳይሆን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ተጠናክሮ መውጣት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ከፊታችን በሚመጡት አገራዊ ምርጫዎች ህዝቡ የሚሰጠውን ውሳኔ በጸጋ ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ምንም ዓይነት

ብዥታና ጥርጣሬ በማይፈጥር ሁኔታ ከወዲሁ በተግባር ማረጋገጥ አለበት፡፡ ከእንግዲህ የኢህአዴግ ጭንቀት እንዴት አድርጌ የስልጣን ዘመኔን ላራዝመው የሚል ሳይሆን መምጣቱ የማይቀረውን የለውጥ ሂደት እንዴት አድርጌ ለአገሪቱም ሆነ ለራሴ የወደፊት ህልውና ዋስትና በሚሰጥ መንገድ እንዲካሄድ ላድርገው የሚል መሆን አለበት፡፡ አሁን አገሪቱ የምትገኝበት ሁኔታ ኢህአዴግ ስልጣን ሲይዝ ከነበረው ሁኔታ በውስጥ ፖለቲካዊ የሃይል አሰላለፍ፣ በአካባቢያዊና አለማቀፋዊ ሁኔታ፣ በህዝቡ የዲሞ-ግራፊክ ስብጥርና እድገት፣ በአጠቃላይም ከህዝቡ ጥቅምና ፍላጎት አኳያ በብዙ ዕርቀት የተለወጠ መሆኑን በማመን ጊዜውንና ትውልዱን ለሚመጥን ለውጥ መዘጋጀት አለበት፡፡ ኢህአዴግ ካለፉት የአገራችን ስርዓቶች በተለዬ ከመንግስት ለውጥ በኋላ ቀጣይ ህልውና እንዲኖረውም ሆነ በበጎ ታሪክ እንዲዎሳ ከፈለገ ብቸኛው መፍትሄ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በመተባበርና በመመካከር ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የሚካሄድበትን ቅድመ-ሁኔታ በአግባቡ አመቻችቶ የህዝቡን ውሳኔ ያለምንም ማቅማማት መቀበል ነው፡፡ ኢህአዴግ ከእንግዲህ አድርባይ ካድሬዎች የሚያቀርቡትን መረጃና የራሱን ጩፀት በራሱ መገናኛ ብዙኃን እያዳመጠ የህዝብ ድጋፍ አለኝ በማለት ራሱን እያታለለ መኖሩን ማቆም አለበት፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሁን ያላቸው ድርጅታዊ ጥንካሬ የወቅቱን የህዝብ ትግል በአግባቡ አቅጣጫ አስይዞ ለመምራትም ሆነ የመንግስት ስልጣን ይዞ ይህንን ሰፊና ውስብስብ ችግር ያለበት አገር ለመምራት እንደማያስችላቸው አምነው በመቀበል ቀዳሚ ትኩረታቸውን የራሳቸውን ድርጅታዊ ጥንካሬ በመፍጠር ላይ ማድረግ አለባቸው፡፡ ተቃዋሚዎች ተገቢውን ድርጅታዊ ጥንካሬ ፈጥረውና አሳማኝ አማራጭ ሃሳብ አቅርበው በህዝብ በመመረጥ ለስልጣን ሊበቁ የሚችሉትም ሆነ የሚያስተዳድሩት አገርና ህዝብ ሊኖራቸው የሚችለው የአገሪቱ ሰላም፣ አንድነትና ህልውና ተጠብቆ ሲቀጥል ብቻ መሆኑን በመረዳት እራሳቸውም ሆኑ ህዝቡ የሚያካሂደው ትግል ፍጹም ህጋዊና ሰላማዊ እንዲሆን የበኩላቸውን የማይተካ ሚና መጫዎት አለባቸው፡፡ በአገራችን ውስጥ ያለው የፖለቲካ ቅራኔ እጅግ ውስብስብ መሆኑን በመረዳት፣ አገራችንም በአፍሪካ ቀንድ የምትገኝበት ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታ በብዙ ችግሮች የታጠረ መሆኑን በመገንዘብ በአገራችን የሚካሄድ ማንኛውም የስልጣን ሽግግር የአገር ህልውናን ጥያቄ ውስጥ በማያስገባ መንገድ ብቻ እንዲካሄድ ማድረግ የተቃዋሚው ጎራ ሃላፊነትም መሆን አለበት፡፡

ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ የአገራችን ችግሮች ብቻ ሳይሆን የዛሬውና የወደፊቱ የአገሪቱ ችግሮች የመፍትሄ አካል መሆኑንም አምነው በመቀበል ከስሜታዊነትና ከፅንፈኛነት በፀዳ መንፈስ ከኢህአዴግ ጋር በመዎያዬትና በመደራደር ህዝቡ በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ የስልጣኑ ባለቤት የሚሆንበትን ዕድል ለማመቻቸትና በመጨረሻም ህዝቡ የሚሰጠውን ውሳኔ ያለማቅማማት ለመቀበል መወሰን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቃዋሚዎች ከታሪክ መማራቸውንም ሆነ ከኢህአዴግ የተሻሉ መሆናቸውን ማሳዬት የሚችሉት እንደተለመደው በኃይል ወይም በሌላ አቋራጭ መንገድ ስልጣን ለመያዝ በሚያደርጉት ጥረት ሳይሆን ህዝቡ በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ የራሱ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን በሚያደርጉት ትግል መሆን አለበት፡፡

የተደራጁ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆኑ የአገሪቱ ባለቤት የሆነውና ፓርቲዎችን በመደገፍና በመቃወም የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርገው ህዝብም የበለጠ ሃላፊነት አለበት፡፡ ህዝቡ ይች አገር በፖለቲካ ቀውስ ምክንያት ወደ መንግስት የለሽነት ወይም የእርስ-በርስ ጦርነት ውስጥ ብትገባ ዋናው ተጎጅ እራሱ መሆኑን በመገንዘብ ከማንም በላይ ለአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ተቆርቋሪና ጠበቃ መሆን ያለበት ህዝቡ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን የተፈጠረው የፖለቲካ ቀውስ ተረጋግቶ የፖለቲካ ሃይሎች በሰከነና በተረጋጋ መንገድ የመዎያየትና የመደራደር ዕድል ካላገኙ በስተቀር ህዝቡ ዞሮ ዞሮ የሚፈልገውን ለውጥ ሊያገኝ አይችልም፡፡ በተለይም ተቃዋሚውን ጎራ የሚደግፈው ህዝብ ፍላጎቱንና አስተሳሰቡን የሚዎክል ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ እስካልፈጠረ ድረስ መንግስትን ከስልጣን በማስወገድ ብቻ ምኞቱን ሊያሳካ አይችልም፡፡ ይህንን እውነታ በውል በመረዳት በአንድ በኩል ለሰከነ ፖለቲካዊ ውይይትና ድርድር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ሰላምና መረጋጋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፍላጎቱንና ጥቅሙን የሚወክልለት ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት መፍጠርን ቀዳሚ አጀንዳው አድርጎ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡

እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሞሉ በግርግርና በነውጥ ሊመጣ የሚችል የመንግስት ለውጥ መንግስት የለሽ የመሆንና መቋጫ የሌለው የርስ-በርስ ጦርነት ውስጥ የሚያስገባ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል በመገንዘብ ፖለቲካዊ ቀውሱን ከሚያባብሱ

ማናቸውም ዓይነት ድርጊቶች ራሱን መቆጠብና ሌሎች የፖለቲካ ሃይሎችም ከተመሳሳይ አውዳሚ ድርጊት ተቆጥበው ትግላቸውን በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲያራምዱ አስፈላጊውን ጫናና ግፊት ማድረግ አለበት፡፡ የህዝቡ አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት የሚለካው አገራዊ አደጋ እንዳይከሰት የሚያደርገውን ጥረት አስቀድሞ በተገቢው ጊዜና ሁኔታ በመፈፀም ነው እንጂ- በሶማሊያ፣ በሩዋንዳ፣ በዩጎዝላቪያ፣ በሊቢያ፣ በየመንና ሶሪያ ሲሆን እንዳዩነው አደጋው ከተፈጠረ በኋላ የታሪክ ተፀፃች በመሆን አይደለም፡፡ ከ 1966 እና ከ 1983 የአገራችን የመንግስት ለውጥ የቅርብ ጊዜ ታሪክ በአግባቡ ተምረን ከሆነም "ኢህአዴግ ይውደቅ እንጂ የመጣው ይምጣ" የሚለው ስሜታዊ መፈክር የትም አያደርሰንም፡፡ እንዲህ አይነቱ ስሜታዊ አስተሳሰብ ተመሳሳይ ታሪክ መድገም ብቻ ሳይሆን እስካሁን አይተነው ለማናውቅ የባሰ አደጋ ሊዳርገን ይችላል፡፡

በእኔ አመለካከት የወቅቱ ችግር ሊፈታ የሚችለው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ጠንካራ ብሄራዊ መግባባትና የእርቅ ስሜት በመፍጠርና ሕዝቡ በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እውነተኛ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን በማድረግ እንጂ በኢህአዴግ ጥልቅ ተሃድሶም ሆነ በጠበንጃና በአመፅ ግርግር አይደለም፡፡ ኢህአዴግ፣ ተቃዋሚዎችና ህዝቡ ከፍ ሲል በተጠቀሰው መሰረት የየበኩላቸውን ሃላፊነት የአገርና የህዝብን ጥቅም በማስቀደም ከተወጡ አገራችንን ከከፋ አደጋ ከመታደግም ባለፈ የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባለቤት እንድትሆን ልናበቃት እንችላለን፡፡ የወቅቱን ስጋትና አደጋም ወደ አንድ ጥሩ የለውጥ እድል ልንቀይረው እንችላለን፡፡

ልደቱ አያሌው

ጥቅምት 2009 ዓ.ም